
# ትንሣኤ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

ቁጥር ፻፵፩

ጥቅምት ፲፱፻፹፩ ዓ.ም



የአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ

ዋጋ ፩ ብር

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጉሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።»

ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ኅሩያን ልሣነ ወርቅ በዛብህ

ም አዘጋጅ መ ክ ?ረ
ርግብ ማርቆስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ፖ. ሣ. 3137
አዲስ አበባ ፤

# ማውጫ

| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| ርእሰ አንቀጽ (አራተኛው ፓትርያርክ) | ፪ |
| የ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. ዘመን መለወጫን ምክንያት በማድረግ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ያስተላለፉት ቃለ ቡራኬ | ፬ |
| ፬ኛው ፓትርያርክ | ፭ |
| የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በዓለ ሢመት ተከናወነ | ፲ |
| እናቱና ክርስቶስ በምን ምክንያት ተሰደዱ | ፲፬ |
| የምሥራች | ፲፯ |
| የቤተ ክርስቲያን ታሪክ | ፳ |
| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ጥቅሶች | ፳፫ |

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በቅድሚያ በእግዚአብሔር ስም መንፈሳዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ። በየወሩ በትንሣኤ መጽሔት እየታተሙ የሚወጡት መንፈሳውያን ጽሑፎች ነፍስን የሚያለመልሙና የሚያረኩ ናቸው ። ወደ ፊት ኃያሉ እግዚአብሔር እንዲያበረታችሁ በመመኘት አንድ ጥያቄን አቀርባለሁ ይኸውም በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ቅዳሴ በሚከናወንበት ገባሬ ሠናዩ ቄስ መንፈሳዊ የሆነ የዓዋጅ ቃል ያነባል ። ቃሉንም እንደሚከተለው አስፍሬዋለሁ ።

"ንጹሕ የሆነ ከቁርባኑ ይቀበል ንጹሕ ያልሆነ ግን አይቀበል ለሰይጣንና ለመልእክተኞቹ በተዘጋጀ በመለኮት እሳት እንዳይቃጠል በልቡናው ቂምን የያዘ ፡ ልዩ አሳብና ዝሙት ያለበት ቢኖር አይቅረብ ይልና" እጁን ከአፍአዊ እድፍ ንጹሕ እንዳደረግሁ እንደዚሁም ከሁላችሁም ደም ንጹሕ ነኝ ብሎ እጁን ይታጠባል ይህ ቃል የማይታበል ቢሆንም እጅግ የሚያስፈራና የሚያስደነግጥ ነው ።

ይህንኑ መንፈሳዊ የዓዋጅ ቃል ጥሶ ንጹሕ ሳይሆን የክርስቶስን ሥጋና ደም የሚቀበል ቢኖር በራሱ ላይ ጥፋትን እንደ ፈረደ በግልጽ የሚታወቅ ነው ከዚህ ላይ ያለኝ አስተያየት ንጹሕ ያለ ክርስቶስ እንደሌለና ሰው የሚድነው በሥራው ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔርም ቸርነት መሆኑን ከቅዱሳት መጻሕፍት እንረዳለን ከመምህራንም እንማራለን ፡

ስለዚህ ሥጋዬን ያልበላ ደሜን ያልጠጣ የዘለዓለም ሕይወትን አያገኝም የሚለውን የጌታችን የመድኃኒታችን ቃል መሠረት በማድረግ ምእመናን ከሥጋውና ከደሙ ርቀው እንዳይቀሩ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ የሚመለሱበት የተለመደው መንፈሳዊ—ትምህርታችሁ በትንሣኤ መጽሔት ተብራርቶ ቢገለጽና ሰባክያነ ወንጌልም በየአሉበት ትምህርት ቢሰጡበት መልካም ነውና ከላይ እንደገለጽኩት በትንሣኤ መጽሔት ሰፋ ያለ ትምህርት ስጡልን ፡ ሰባክያነ ወንጌልም በትጋትና በንቃት እንዲያስተምሩ አሳስቡልን በማለት ጥያቄዬንና አስተያየቴን አጠቃልላለሁ ።

ባለምባራስ በቀለ ደንበለው
አርሲ ሀ/ ስብከት ኮፈሌ

መልስ ባላምባራስ በቀለ ደንበለው ስላቀረቡልን ሰላምታ አጸፋውን በመስጠት ላቀረቡት ጥያቄ መልስ እንሰጣለን እርስዎ እንደገለጹት ማንኛውም ሰው ከኃጢአት ንጹሕ አይደለም ነገር ግን ጥቃቅንና ታላላቅ ኃጢአት አለ ። ጥቃቅን ኃጢአት የሚባለው በሀልዮ የሚፈጸመው ነው በገቢር የሚፈጸመው ኃጢአት ግን ታላቅና ከባድ ነው ፡

ሥጋውንና ደሙን ከመቀበል በፊት ከኃጢአት መንጻት ያስፈልጋል ። መንጻትም የሚቻለው በንስሐ ስለሆነ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ሥጋውንና ደሙን ለመቀበል ከመቅረቡ አስቀድሞ የሠራውን ኃጢአት ሁሉ ለመምህረ ንስሐው መናዘዝና ከመምህረ ንስሐው የሚሰጠውን ቀኖና በጥንቃቄ የመፈጸም መንፈሳዊ ግዴታ አለበት ።

ከኃጢአት ነጽቶ ከተቀበሉት ለመንግሥተ ሰማያት ያበቃል በሥጋ ቢሞቱ በነፍስ ሕያው አድርጎ ለዘለዓለም እንዲኖሩ ያደርጋል ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ይህንን ሲያስረዳ ሥጋዬ እውነተኛ መብልና ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና ሥጋዬን የበላና ደሜንም የጠጣ በእኔ ይኖራል ። እኔም በእርሱ እኖራለሁ ። ብሏል ዮሐንስ ፮ ፡ ፶፭—፶፮ ነገር ግን ከኃጢአት ሳይነጹ ቢቀበሉት ፍዳን የሚያመጣ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ሰውም ራሱን ይፈትን እንዲሁም ይህንን ኅብስት ይብላ ይህንም ጽዋ ይጠጣ ሳይገባው ግን የክርስቶስን ሥጋ ቢበላ ደሙንም ቢጠጣ ለራሱ ኩነኔን ይበላል ይላል ፩ኛ ቆሮ ፲፩·፳፰

ቄሱ በቅዳሴ ጊዜ እጁን እየታጠበ ለምእመናን የሚያስተላልፈውም ቃል ምእዳን የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል መሠረት በማድረግ ነው እንጂ ከራሱ አንቅቶ አይደለም ።

ስለዚህ ቃሉ ለምእመናን አስፈሪና አስደንጋጭ ነውና አይነገር አይሰማ ማለት አይቻልም ደግሞም ሰው ሁሉ ከኃጢአት ንጹሕ ሊሆን አይችልምና ንስሐ ሳይገባ የክርስቶስን ሥጋና ደም ይቀበል ሊባልም አይገባም እንግዲህ ጠያ
(ወደ ገጽ ፲፯ ዞሯል)



www.ethiopianorthodox.org

(ርእሰ አንቀጽ)

# አራተኛው ፓትርያርክ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በበላይ ሆነው የሚመሩና የሚያስተዳድሩ **አራተኛው ፓትርያርክ** ነሐሴ ፳፬ ቀን ተመርጠው ነሐሴ ፳፱ ቀን ፲፱፻፹ ዓ.ም የፓትርያርክነቱን ሥልጣን **ተቀብለው በመንበረ ፓትርያርክ ተቀምጠዋል ።**

በዚህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከፍ ያለ ደስታ ተሰምቷታል ። ቤተ ክርስቲያናችን ይህንን ዓቢይ ክብር ለመቀዳጀት በየጊዜው ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎች ጋር ታላቅ ተጋድሎ ስታደርግ ኖራለች ። ግብፃውያን መንፈሳውያን አባቶች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ የነበራቸው ተጽዕኖ ፲፮፻ ዓመት በላይ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም ።

ይሁን እንጂ ይህንን መንፈሳዊ ተጽዕኖ ለማስወገድ ከመጣር ያቋረጠችበት ዘመን አልነበረም ። አንዳንድ ጊዜ ነገሥታቱ ሳይቀሩ ለዚህ መንፈሳዊ ዓላማ መሳካት የተጋደሉበት ክፈለ ዘመን ይገኛል ። ለምሳሌ በ፬ኛው ምዕተ ዓመት የነበረው ቅዱስ ሐርቤ ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አባቶች ተመርጠው ተሹመው እዲያስተምሩ ከፍተኛ ጥረት አድርገ ሳይሳካለት እንደቀረ በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል ።

በኋላም ፩ኛው ዮሐንስ የቅዱስ ሐርቤን ዓላማ በመከተል ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ተመርጠው ጳጳሳት እንዲሾሙ ፡ ለግብፃውያን መንፋሳውያን አባቶች ጥያቄ አቀረበው ነበር ፡ ነገር ግን ኢትዮጵያውያን ጵጵስና የተሾሙ እንደሆነ የአንበጣ መንጋ ፡ በረዶ ፡ አይጥ ወዘተ አዝመራውን ያጠፋዋል ፡ ሕዝቡ በመቅሠፍት ያልቃል ፡ አባሩ ቸነፈሩ ፡ ይጸናል እየተባለ በግብፃውያን ይሰበክ ስለነበረ ከኢትዮጵያ ምሁራን ጵጵስና እንዳይሾሙ በሩን ግጥም አድርጉ ዘግቶ ሽንጡን ገትሮ ይታገል የነበረው የግብፃውያን ተንኮል ያልገባው ኢትዮጵያዊ ነበር ።

"ቀን ሲደርስ አምባ ይፈርስ" እንደሚባለው "ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር" እግዚአብሔር ሥራውን የሚሠራበት የተወሰነ ሰዓት አለና አምላክ ፈቃዱ በሆነ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያለማቋረጥ ያደረገችው ተጋድሎ ሠምሮ በ፲፱፻፳፩ ዓ.ም የመጀመሪያዎችን ጳጳሳት ከራሷ ሊቃውንት መርጣ ለማሾም በቃች ።

የመጀመሪያዎቹ ተሿሚዎችም ፬ ሲሆኑ እነርሱም ፡

፩ ብፁዕ አቡነ አብርሃም የሬት ስማቸው መምህር ደስታ ፡

፪ ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ የሬት ስማቸው መምህር ወልደ ኪዳን ፡

፫ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ የመጀመሪያ ስማቸው መምህር ኃይለ ማርያም ፡

፬ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል የመጀመሪያ ስማቸው መምህር ሐዲስ ናቸው

ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሔዳል "እንደሚባለው በጳጳሳት የተጀመረው ሥልጣን መንፈሳዊ ዕድገትን አገኝቶ ዛሬ ከፓትርያርክ ደረጃ ደርሶ ሲታይ ኢትዮጵያዊ ክርስቲያን ለሆነ ሁሉ ከፍ ያለ መንፈሳዊ ኩራት ይሰማዋል ።

ቤተ ክርስቲያናችን የፓትርያርክነ ሥልጣን ለራሷ ገንዘብ አድርጋ ኢጲስ ቆጶሳትን ጳጳሳትን ሊቃነ ጳጳሳትን መሾም ከጀመረች እንሆ ፴ ዓመት ሲሆን ሦስት አባቶች ተሾመው ከእግዚአብሔር ተወስኖ በተሰጣቸው ዕድሜ የሚገባቸውንና የተቻላቸውን ያህል እየሠሩ አልፈዋል ።

አሁን የተሾሙት ፬ተኛው ፓትርያርክ መሆናቸው ነው ። እርሳቸውም ነሐሴ ፳፬ ቀን ተመርጠው ነሐሴ ፳፱ ቀን ፹ ዓ/ም የተሾሙት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ናቸው ። ቅዱስነታቸው ለውድድር ከቀረቡት ሦስት ሊቃነ ጳጳሳት መካከል ከፍተኛውን ድምፅ በማግኘት የ፬ኛውን መንበረ ፓትርያርክነት ሥልጣን ተቀዳጅተዋል ።

ይህ ክብር ፡ ይህ ሥልጣን ፡ ይህ መዓረግ ለአንድ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን አባት ብቻ የተሰጠ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ ሁሉ የተሰጠ ታላቅ ክብር ነው ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን ለዚህ ታላቅ ክብር ካበቋቸው ዋና ዋና ተግባሮች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ፡



፩ኛ መንፈሳውያን አዳሪ ትምህርት ቤቶች እንዲከፈቱ ፡

፪ኛ የካህናት ማሠልጠኛዎች እንዲቋቋሙና ካህናት በተግባረ ዕድ እንዲሠለጥኑና ኑራቸውን እንዲያሻሽሉ ማድረጋቸውና ምንም መተዳደሪያ ያልነበራቸው የቤተ ክርስቲያን የአብነት መምህራን የወር ደመወዝ እንዲኖራቸው ቅዱስነታቸው በማድረጋቸው ለሊቃውቱ ከፍ ያለ ደስታ ተሰምቷቸዋል ።

እንዲሁም ያስተዳድሩት በነበረው በጎንደር ሀ/ ስብከት ፵፲ አብያተ ክርስትያናት የተተከሉ ሲሆኑ ለ፫፻፳ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ ዕድሳት ተደርጓላቸዋል ፡

ወደ ልማትም ተግባር መለስ ብለን የተመለከትን እንደሆነ በርከት ያሉ የልማት ተግባሮች እንደተከናወኑ እናገኛለን ። ለዚህም በየገዳማቱና በየአድባራቱ የተተከሉት ወፍጮዎች ጥንታውያን መጻሕፍት በብራና እንዲጻፉ ያደረጉት ፡ ጥረት እንዲሁም በጋደንት በእስቴ ወረዳ የችግኝ ጣቢያዎችን አቋቁመው በየዓመቱ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ችግኞች በየአብያተ ክርስቲያናቱ አካባቢ እንዲተከሉና ለሕዝባውያን ድርጅቶች እንዲከፋፈሉ ብማድረግ የተራቆተችው መሬት ደን እንድትለብስ አድረገዋል ።

ቅዱስነታቸው በተጨማሪ ለስብከት ወንጌል ለሰነበተ ት/ቤት ለዳራሾች በየአብያተ ክርስቲያኑ አካባቢ ለሠርተዋል ። ከዚህ ጋር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ደንብ ቃለ ዓዋዲ በትክክል እንዲፈጸም በማድረጋቸውና ሰበካ ጉባኤንም በሚገባ በማጠናከራቸውና በየዓመቱ በሚደረገው በሀገር አቀፍ ሰበካ ጉባኤ የሥራ ግምገማ በተደረሰበት አጥጋቢ ውጤት የጎንደር ሀ/ ስብከት ከሌሎች አህጉረ ስብከት ከፍተኛውን ደረጃ እንዲይዝ አስደርገዋል ።

በዚህ መሠረት በተከታታይ የሚከተሉት ከፍተኛ የሆኑ ውጤቶች ተመዝግበዋል ።

በ፲፱፻፸፮ ዓ.ም አንደኛ

በ፲፱፻፸፯ " አንደኛ

በ፲፱፻፸፯ " አንደኛ

በ፲፱፻፸፰ " አንደኛ

በ፲፱፻፸፱ ሁለተኛ በአጠቃላይ ሀ/ስብከታቸው በተከታታይ ፬ ጊዜያት በአንደኛ ደረጃ ሲሸለም አንድ ጊዜ የሁለተኛ ደረጃን በማ ግኘት እንዲሸለም አድርገዋል ።

እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉት ሕያዋን ተግባሮቻቸው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን ለዚህ እጅግ በጣም ከፍተኛ ለሆነው የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን መዓርግ አብቅተዋቸዋል ። ቅዱስነታቸው ሠርቶ የማሠራት ልምድ ስላላቸው ከአሁን ቀደም ከሠሩት ሥራ የበለጠ ሠርተው በማሠራት ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ ዕድገትን እንደሚያስገኙላት እንተማመናለን ።

ነቢዩ ኢሳይስ "የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮህ የሰው ድምፅ አዘቅቱ ሁሉ ይሙላ ተራራውና ኮረብታውም ዝቅ ይበል ጠማማውም የቀና መንገድ ይሁን ሸካራውም መንገድ ትክክል ይሁን ሥጋን የለበሰ ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን ይይ" ብሎ እንደተናገረው ፡ አራተኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የተሐድሶ መንገድን በመጥረግ የተዛባውን የሚያስተካክሉ የጠመመውን የሚያቀኑ ከትምህርት ማጣት የተነሣ የተራቆተውን ልብ በትምህርተ ወንጌል የሚያለመልሙ ቅዱስ አባት በመሆናቸው የሚሰጡትን መንፈሳዊ መመሪያ እየተከተሉ በመሥራት ቤተ ክርስቲያናችንን ካለባት ችግር ፈጽሞ ለማላቀቅ ተግቶ መሥራት የማንኛውም ምእመን ዓላማ ሊሆን ይገባል ።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ...

(ከገጽ ፳፱ የዞረ)

በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር አብ ይጠራባቸው የነበሩ ስሞች እግዚአብሔር ወልድም የሚጠራባቸው ሆነው ተገኝተዋል ። ማስረጃ

ኢሳ.፱.፮ ክርስቶስ "ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት (አበ ዓለም ሐዲስ)" ተብሎ ተጠይ ሟል ። ዘፀ.፫.፲፬ የነበረውና ያለው (ዘሀሎ ወይሄሉ" የሚለው ስመ አምላክ በዮሐንስ ፰ በቁጥር ፶፬ ፶፰ ላይ እኔ የነበረሁና ያለሁ" በማለት ደጋግሞ ለአይሁድ ከነገ ራቸው በኋላ በመጨረሻ ቁጥር ፶፰" እምቅድመ አብርሃም ሁሎኩ እነ እኔ ከአብርሃም በፊት ነበርኩ በማለት ዘለዓለማዊ የባሕርይ አምላክ መሆኑን አስረድቷል



www.ethiopianorthodox.org

[illegible]

# ምክንያት በማድረግ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ያስተላለፉት ቃለ ቡራኬ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ።

በከተማና በገጠር ፡ በመሀል ሀገርና በጠረፍ ፡ በባሕርና በየብስ፡ በሥራ ላይ ላላችሁ ፡ በሕመም ምክንያት በሐኪም ቤት የምትገኙ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ከዘመናት በፊት የነበረ ፡ በዘመናት መካከል ያለና ዘመናትን አሳልፎ የሚኖር አምላካችን እግዚአብሔር እንኳን ለሺህ ጠኝ መቶ ሰማንያ አንድ ዓመተ ምህረት በሰላም አደረሳችሁ ።

"ይትባረክ ስሙ ለእግዚአብሔር ለዓለም ወእስከ ለዓለም እስመ ሎቱ ውእቱ ጥበብ ወምክር፡ ወኃይል ። ወውእቱ ይዌልጥ ዓመታተ ወመዋዕለ ።

የእግዚአብሔር ስሙ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ይክበር ይመስገን ። ጥበብና ምክር ኃይልም የእርሱ ገንዘቦች ናቸውና እርሱም ዓመታትንና ጊዜያትን ይለውጣል" (ዳንኤል ፪ ፡ ፳፩)

እግዚአብሔር የሰው ልጅ ዓመታትን በአውራህና በዕለታት በሰዐታትና በደቂቃ ለመቁጠር እንዲችል ጥበብን ስለሰጠው ፡ በጊዜ ሥራን ሠርቶ ፡ ታሪክ እንዲያስመዘግብ ኃይልን ስለአደለው ሁል ጊዜ ሊመሰገን ይገባል ። እግዚአብሔር ሥራ ያልሠራበት ጊዜ የለም ። ሰውም በእግዚአብሔር ምሳሌ ስለተፈጠረ ጊዜን ያለሥራ ሊያሳልፍ አይገባውም ።

ዓለም ሲፈጠር ከጊዜ ጋር ነው ። ከዓለም በፊት ጊዜ አልነበረም ። እግዚአብሔር ጊዜን በሥራ ለሥራ ፈጠረ ዓለም ሲፈ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ከመርቆሬዎስ ቃለ ቡራኬ ሲያደርጉ

ጠር ጊዜ አንድ ተብሎ ተጀመረ ። በዚህ መሠረት ጊዜ ለሥራ መሆኑን እንገነዘባለን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ጊዜ ሳለን መልካም ሥራ እንሥራ" ይላል ። ሰው ያልነበረበት ጊዜ እንደነበረ የማይኖርበት ስለሚኖር ዛሬ ባለው ጊዜ ሥራ መሥራት ይኖርበታል ።

ለሀገር ዕድገት ልማትና ብልጽግና ለሕዝብ ጥቅምና በረከት ፡ ዕውቀትና ጤንነት ለመሥራት ጊዜን በሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል ። "ለሁሉም ጊዜ አለው" ቢባልም በመርሐ ግብር መሥራትን ያመለክታል እንጂ የሰው ልጅ ተቀምጦ የተፈቀደውን የሥራ ጊዜ ያለ ሥራ ማሳለፍ አይኖርበትም ።

ስለዚህ የተወደደው ሰዓት የተመረጠውም ዕለት ዛሬ ነው ።

ስለሆነም የሰው ልጅ ሁሉ በሕይወት ዘመኑ ለመልካም ሥራ መትጋትና ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለማገኘት የሚያበቃውን መሥራት ይኖርበታል ።

ዛሬ ያለንበት ዓለም ጦርነትና ጥላቻ የበዛበት ሆኖ ይታያል ። አብዛኛው የዓለም ሕዝብ በረኀብ በበሽታ በእርዛት በድንቁርና ይሰቃያል ። ስለዚህ የዓለም መሪዎችና የአብያተ ክርስቲያን መሪዎች እያንዳንዱም ኅብረተሰብ የዓለም ሰላም የሚገኝበትን ሁኔታ ረኀብ በሽታ ፤ ጦርነትና ድንቁርና የሚወገዱበትን መንገድ የመቀየስ ኃላፊነት አለባቸው ። ለዚህም ሁሉ ጥበብን ምክርን ኃይልን የሚሰጥ እግዚአብሔር ስለሆነ እርሱን በእምነትና በጸሎት መጠየቅ ከሁሉ የበለጠ ጥበብ ነው ።

ቤተ ክርስቲያንም ሁልጊዜ ስለ ሰላም እግዚአብሔርን ትለምናለች ስለ ሰላም ጸልዩ እያለች የሰላም ዕቅዷን ታውጃለች ሰላም ማለትም ፤ አንድነት ፤ እኩልነትና ነፃነት ነው ። በዓለም ላይ ያለው የሰው ልጅ ነፃነት እኩልነትና መብት ካልተጠበቀ ፍትሕና ርትዕ ከሌለ ሰላም ሊኖር አይችልም ፤ የሰው ልጅ ለራሱ ሊደረግለት የሚፈልገውን ለሌላው ካላደረገ በራሱ ሊደረግበት የማይፈልገውንም በሌላው ላይ ከማድረግ ካልተቆጠበ ሰላም በዓለም ላይ አይገኝም ።

ስለዚህ የሰላም መሠረት የሆነው እኩልነት ፡ ፍትሕና ርትዕ ፡ ባልንጀራን እንደራስ መውደድ በዓለም ላይ እንዲኖር ቤተ ክርስቲያን ዘወትር ያለማቋረጥ ትጸልያለች ትመክራለች ፡ ታስተምራለች።

በአዲሱ ዓመት ከዓለማችን ረኀብና ችግር ጦርነቶች ሁሉ ተወግደው ብልጽግና በረከት ፤ ሰላምና ፍትሕ እንዲሰፍን የሰላም አምላክ እግዚአብሔር ለዓለም ሰላምን ፍቅርንና አንድነትን ይስጥልን ።

ዘመኑን የሰላምና የጤና የበረከትና የደስታ ዘመን ያድርግልን ።

ሀገራችን ኢትዮጵያን ለዘለዓለም ይባርክልን ።

አሜን ።

፩ኛው ፓትርያርክ

# ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው ተመረጡ

ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ ለውድድር ከቀረቡት ሦስት ሊቃነ ጳጳሳት መካከል ከፍተኛ ድምፅ በማግኘት የተመረጡት ነሐሴ ፳፪ ቀን ፲፱፻፹ ዓ/ም መሆኑ ታውቋል።

ከዚያ ቀደም ሲል ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት ፱ አባላት የሚገኙበት አስመራጭ ኮሚቴ ተቋቁሞ በእጩነት መቅረብ የሚገባቸውን ፫ ሊቃነ ጳጳሳት በቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግና ሥርዓት መሠረት ውድድር አቅርቦ የድምፅ መስጠቱ ሥነ ሥርዓት ከ፱—፲ ሰዓት ዲሞክራሲያዊ በሆነ አሠራር መፈጸሙን ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊና የአስመራጭ ኮሚቴው ሊቀ መንበር ገልጸዋል ።

የምርጫው ሥነ ሥርዓት ከላይ እንደተገለጸው በዚሁ ዕለት ከሰዓት በፊት ከተፈጸመ በኋላ የድምፅ ቆጠራው መርሐ ግብር ቀጥሎ ፲ ሰዓት ሲሆን ብፁዕ አቡነ አብርሃም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ዓቃቤ መንበረ ፓትርያርክ ፡ ብፁዐን ሊቃነ ጳጳሳት ሊቀ ማዕምራን ድምፀ ገ መድኀን የጠ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ አስመራጭ ኮሚቴዎችና የምርጫው ተሳታፊዎች በተገኙበት በስብከተ ወንጌል አዳራሽ ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ ንግግር አድርገዋል ፡

## የብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ ንግግርም ነው።

ብፁዕ አቡነ አብርሃም ዓቃቤ መንበረ ፓትርያርክ !

ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት!

ክቡር የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ !

ክቡር የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ደመንበረ ፓትርያርክ ጠ/ ጽ/ቤት የመምሪያና የክፍል ኃላፊዎች የየ





www.ethiopianorthodox.org

አህጉረ ስብከት ሊቃነ ካህናት ፡ የካህናትና የምእመናን ተወካ ዮች፡ የገዳማትና የአድባራት አስ ተዳዳሪዎች በአጠቃላይ ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ጋር የቤተ ክርስ ቲያን አካላት ሁናችሁ አራተኛ ውን ፓትርያርክ ለመምረጥ የተሰ በሰባችሁና በዛሬው ዕለት እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ እንደአንድ ልብ መካሪ ሁናችሁ የቤተ ክርስ ቲያን አባታችሁን በመምረጥ ባለ ታሪክ የሆናችሁ ሁሉ እንኳን ደስ አላችሁ ካሉ በኋላ ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ ንግግራቸውን በመቀጠል አቡነ አብርሃም የመንበረ ፓትርያ



ሊቀ ማዕምራን ደምፀ ገ መድኅን የምርጫ ካርድ ሲያስቀምጡ

ርክ ተጠባባቂ (ሊቀ ጳጳስ)! ቤተ ክርስቲያናችን በዓለም እንደሚ ገኙ አብያተ ክርስቲያናት ከሊቃ ውንቶቿ መካከል መንፈሳዊ አባ ትን እየመረጠች በመሾም ክብርን ከተቀዳጀች ብዙ ዘመናት ሲሆን እነሆ አሁን ከሦስተኛው ወደ አራ ተኛው አባት በመሸጋገር ላይ እን ገኛለን ።

ለዚህ ጥናትና ዝግጅት ቅ ሲ ኖዶስ ሐምሌ ፳፰ ቀን ፲፱፻፹ ዓ/ም ባደረገው አስቸኳይ ስብሰባ በመንበረ ፓትርያርክ ተዘጋጅቶ

የቀረበውን አዲስ የፓትርያርክ ምርጫ ደንብ አጽድቆና ኮሚቴ አቋቁሞ ኃላፊነትን ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ ኮሚቴው የተጣለበ ትን አደራ ለመወጣት ደረጃ በደ ረጃ ተግባሩን በማከናወን እነሆ በዛሬው ዕለት ምርጫው ተፈጽሞ ዝርዝር ዘገባውን የያዘ የኮሚቴውን ውሳኔ ለብፁዕነትዎ አቀርባለሁ በዚሁ የምርጫ ውጤት ውሳኔ መሠረት ለቅዱስ ሲኖዶስ አባላ ትና ምእመናን ንግግር በማድረግ ከፍተኛ ድምፅ አግኝተው ለ፬ተ ኛው የፓትርያርክነት መዓርግ የበ ቁትን አባት እንዲገልጹላቸውና

እንዲያስታውቋቸው በቅዱስ ሲኖ ዶስና በአስመራጭ ኮሚቴው ስም እጠይቃለሁ በማለት ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ ንግግራቸው አጠቃለ ዋል።

ቀጥሎም ብፁዕ አቡነ አብር ሃም ዓቃቤ መንበረ ፓትርያርክ የሚከተለውን ንግግር አድርገ ዋል።

## የብፁዕ አቡነ አብርሃም ንግግር

"…እኩት እግዚአብሔር ዘወ ጠጠ መጽሐፈ ዕዳነ በክሂሎቱ ፡ ወነሠተ አረፍተ ማዕከል አንተ ጽልዕ በሥምረቱ ለብዙ ዘመናት በሥርዋፅ ተጽፎብን የኖረውን የዕዳ ደብዳቤያችን በከሃሊነቱ ደመሰሰልን ፡ በግብፅና በኢትዮ ጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክር ስቲያን መካከል የነበረውን የጥ



ብፁዕ አቡነ አብርሃም አቃቤ መንበረ ፓትርያርክ ሆነው ለጸዓ ቀናት የሰነበቱት

ላቻ ግድግዳ በፈቃዱ አፈረሰልን ፡ ከዓለም ክርስቲያኖች መሪዎችና አባቶች ጋር በእኩልነት ለመኖ ርና በመብት ለመጠቀም ያበ ቃን ልዑል እግዚአብሔር ይክ ብር ይመስገን ብለዋል

ብፁዕነታቸው ንግግራቸውን በመቀጠል ቀደም ሲል በነቢዩ በኤርምያስ ··እወዲ ሕግዩ ውስተ ልቦሙ ወእጽሕፎ ውስተ መጽሐ ፎሙ·· ሕጌን በልቡናቸው አሳድ ረዋለሁ በሕሊናቸውም እጽፈዋ ለሁ ብሎ እግዚአብሔር አምላክ ያናገረውን ለመፈጸም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ የሆነችውን አዲሷን ሕግ በምእመናን ልቡና አመቻ ችቶ ሲያኖር … እናንተስ ሁላች ሁም ወንድማማቾች ናችሁ ከእና ንተ በላይ ሊሆን የሚወድ ቢኖር ሎሌ አገልጋይ ይሁናችሁ … በማ ለት እኩልነትን አስተማረ እንጂ



የጣት ያህል ብልጫ እንዲኖር አላደረገም፡ የግብፅ ቤተ ክርስቲ ያን ግን የተንኮል ስንጥር (ሥር ዋፅ) በመብት ዓይናችን ላይ አስገ ብታ የቤተ ክርስቲያንን ደገኛ ክብር እንዳናይ አሳውራን እንዳና ገኝ ነፍጋን በሺህ የሚቆጠሩ ዓመ ታትን አሳልፋብናለች ቤተ ክርስ ቲያናችንም ከዓለም ክርስቲያኖች ጋር በእኩልነት እንዳትራመድ ብቸኛ አድርጋት ኑራለች ፡

ይሁን እንጂ መክብብ ፫፡፩…ከ ሰማይ በታች ላለ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው … እንዳለው እግዚአብ ሔር የፈቀደው ጊዜ ሲደርስ እነሆ ራስን ችሎ መሾም ቀርቶ ከመሾም ዓለም ውጭ የነበረችው ቤተ ክር ስቲያናችን ሙሉ መብት በማግ ኘቷ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታ የምትኖረው የሀገራችን ኢትዮጵያ ጸሎቷ ቅደመ እግዚአብ ሔር ደርሶላት የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነውን አራተኛውን ፓትር ያርክ መርጣ ለመሾም በቃች ስለ ዚህ ለእግዚአብሔር ክብር ምስ ጋና ለእኛ ለልጆቿ መንፈሳዊ ልዕ ልና ይሁን ካሉ በኋላ እንግዲህ በምድር ላይ በመንፈሳዊ ዓለም ከዚህ የበለጠ ሌላ ምን ክበር አለ ·· አልቦ ዘይኄይስ እምዝ ሕግ·· ከዚህ የሚበልጥ ምንም ነገረ የለም ገላ ፭·፳፫·· እንከስ ብኩርና ለነ·· እንግዲህስ ወዲህ መንፈሳ ዊው ሥልጣን የእኛ ነው እያልን መንፈሳዊ ደስታችንን በዓለም ዙሪያ ማሠራጨት እንችላለን በማለት ከአስመራጭ ኮሚቴ ተዘ ጋጅቶ የቀረበውን የምርጫ ውጤት በንባብ አስምተዋል = ቃሉም የሚከተለው ነው ።

፩·ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ የኮሚ ቴው ሰብሳቢ

፪. ብፁዕ አቡነ መርሐ ክርስ ቶስ አባል

፫· ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም አባል

፬· ብፁዕ አቡነ ገበርኤል አባል

፭· ሊቀ ማዕምራን ደምፀገ መድኅን አባል

፮· ፀባቴ እሸቴ ዱባለ አባል

፯· መልአከ ታቦር ተሾመ ዘር ይሁን አባል

፰. አቶ ባይርኩ ገብረ ክርስቶስ አባል

፱· አቶ ጌታቸው ዘሩ አባል ሲሆኑ

አራተኛውን ፓትርያርክ ለመም ረጥ ሲካሄድ የሰነበተው ዝግጅት ነሐሴ ፳፪ቀን ፲፱፻፹ ዓ/ም በመን በረ ፓትርያርኩ በተደረገው ምርጫ ተፈጽሟል ።

## የምርጫው ተሳታፊዎች



ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊና የአስመራጭ ኮሚቴ ሰብሳቢ

፩· የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ፡ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት

፪· የመንበረ ፓትርያርኩ አጠቃ ላይ ሰበካ ጉባኤ አባላት

፫· ከመላው አህጉረ ስብከት የተ ላኩ የካህናትና የምእመናን ተወካ ዮች

፬· የገዳማትና የአድባራት ተወካ ዮች

፭· አጠቃላይ የሰንበት ት/ ቤት ተማሮች ተወካይ ናቸው

እነዚህ የተጠቀሱት ክፍሎች ተገ ኝተው በመንበረ ፓትርያርክ ምር ጫውን አከናውነዋል ። መምረጥ ከሚገባቸው 109 ሰዎች መካከል አሥሩ በልዩ ልዩ ምክንያት አልተ ገኙም ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት መካከል ለአራተኛው ፓትርያርክ ነት ዕጩ ሆነው ለምርጫ የቀረ ቡት ሦስት ሊቃነ ጳጳ ሳት፡—

ሀ· ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል

ለ· ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ

ሐ· ብፁዕ አቡነ ገሪማ ሲሆኑ የድምፅ መስጠቱ ሥነ ሥርዓት እንዳበቃ የድምፅ መስጫው ካርድ በኮሚቴው አባላት ተቆ ጥሮ ፡

፩ ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ ………………፷፮ ድምፅ

፪/ ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ፳፩ ድምፅ

፫/ ብፁዕ አቡነ ገሪማ … ፲፪ ድምፅ ማግኘታቸው ተረጋግ ጧል ፡

በዚህ ምርጫ መሠረት አራተ ኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ህዶ ቤተ ክርቲያን ፓትርያርክ እንዲሆኑ በከፍተኛ ድምፅ የተመ ረጡት ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ መሆናቸውን አረጋግጠን የምር ጫው ውጤት ለብፁዕ አቡነ አብ ርሃም ዓቃቤ መንበረ ፓትርያርክ እንዲቀርብ ተስማምተናል

<u>የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት…</u>

ቀጥሎም ብፁዕ አብርሃም ከአስመ ራጭ ኮሚቴ የቀረበውን ይህንን ቃለ ጉባኤ አንብበው ሲያበቁ የመርሐ ግብሩ ፍጻሜ ሆኗል ።



www.ethiopianorthodox.org

# የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬ ዎስ በዓለ ሢመት ተከናወነ

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ሢመት የተከናወነው ነሐሴ ፳፱ ቀን ፲፱፻፹ ዓ/ም የኢትዮጵያ ርእሰ ከተማ በሆነችው አዲስ አበባ በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ነው ።

ቀድሞ ሲል ከመንበረ ፓትርያርክ ጠ/ጽ/ቤት በወጣው መርሐ ግብር መሠረት ካህናቱ ከሌሊቱ ፤ ሰዓት ጀምረው በቤተ ክርስቲያን በመገኘት ስብሐተ እግዚአብሔር ሲያደርሱ አድርዋል ።

ከጧቱ ፲፪ ሰዓት ጀምሮ የአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎች ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ቀሳውስትና ዲያቆናት ጥንግድርብ የለበሱ መዘምራን ከሰንበት ት/ቤቶች የተወጣጡ ተማሮች ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ምእመናንና ምእመናት የተመደበላቸውን ቦታ መያዝ ጀምረዋል ።

አንድ ሰዓት ከሩብ ሲሆን ጸሎተ ቅዳሴው ተጀምሯል ጸሎተ ቅዳሴው የተካሄደው በሦስቱም መናብርት ሲሆን የተመራውም በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ነበር የመሩትም

፩· ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የጎጃም ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ

፪· ብፁዕ አቡነ መርሐ ክርስቶስ

፫· ብፁዕ አቡነ ገብርኤል

፬· ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ

፭· ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ

፮· ብፁዕ አቡነ ማትያስ ናቸው።

ለሁለት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን አዲሱ ተመራጭ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በብፁዓን ሊቃ ጳጳሳት ታጅበው፥ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሲደርሱ የአብያተ ክርስቲያናት ደወሎች ለ፲ ደቂቃ ያህል ድምፃቸውን አሰምተዋል ።

በካቴድራሉ ግቢ ተሰልፈው ሲጠባበቁ የነበሩ ቀሳውስትና ዲያቆናት መዘምራንና የሰንበት ተማሪዎች ምእመናንና ምእመናት በዝማሬ በልልታና በጭብጨባ ተቀብለዋቸዋል ። ቅዱስነታቸው ወደቅድስተ ቅዱሳኑ ገብተው አጠር ያለ ጸሎት ካደረጉ በኋላ በተዘጋጀላቸው መንበረ ክብር እንደተቀመጡ ሞጣህት ለብሰው በሰልፍ የቆሙ መዘምራን እግዚአብሔር አምላክነ የሚለውን ያሬዳዊ ድርሰት በዜማ አሰምተዋል ወዲያው የሥርዓተ ሢመቱ ጸሎት በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ተጀምሮ አል ።

ጸሎተ አልባስ

ጸሎተ አክሊል

ጸሎተ አርዌ ብርት ተጸልዮ አዲሱ ፓትርያርክ የተዘጋጀውን ልብስ ለብሰው አክሊሉን በመቀዳጀት አርዌ ብርቱንም ተቀብለዋል ። አቃቢ መንበረ ፓትርያርክ ሁነው ለ፹፱ ቀናት የሰነበቱት ብፁዕ አቡነ አብርሃም የሚከተለውን ንግግር አድርገዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ !



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የፓትርያርክነት አክሊልን ሲቀዳጁ

ብፁዕ ሆይ!


ቤተ ክርስቲያን የሕይወት መሠረት እንደመሆኗ ከመሥራቿ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጀምሮ ያለማቋረጥ መንፈሳዊ ተልኮዋን እየፈጸመች እስከጊዜያችን ስትራመድ ትገኛለች ። አበው ቢያልፉ ውሉድ እየተተኩ ያንኑ ፈለግ በመከተል እየሠሩ እነሆ አገራችንን የክርስቲያን ደሴት ሲያሰኟት ይገኛሉ ።



አሁን በክብር በአረፉት ፓትርያርካችን በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ዕረፍት አዝነን ኀዘንን የተመላን ብንሆንም የመንፈስ ቅዱስ ማኅደር የሆነችው ቤተ ክርስቲያን መንበሯ መካን ሆኖ እንዲቀር እግዚአብሔር ባለመፍቀዱ በቅዱስ ሲኖዶስ ጸሎትና መንፈሳዊ ተግባር አርቶዶክሳውያን በሆኑ ካህናትና ምዕመናን ተሳታፊነት መንበሩን ለመውረስ መንፈስ ቅዱስ የመረጠውን ለመተካት ምርጫ ሲካሄድ መቆየቱ የታወቀ ነው ፡ በዚህም መሠረት በተደረገው የፓትርያርክነት ምርጫ ለ፬ኛ ፓትርያርክ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስነትዎን መርጦ ስለሰጠን ቤተ ክርቲያናችን ዛሬ ታላቅ በዓል ታደርጋለች።

በዚህም አጋጣሚ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላትን ፡ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላትን በመራጭነት የቀረቡትን ካህናትና ምእመናን እንኳን ሥራችሁን እግዚአብሔር አሠመረላችሁ እንኳን ደስ አላችሁ ምርጫው መንፈስ ቅዱስን መሪ በማድረግ በትክክልና በእውነት እንደተከናወነ አረጋግጣለሁ።

ቅዱስነትዎንም እንኳን ፬ኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ለመሆን አበቃዎ በማለት በቅዱስ ሲኖዶስና በራሴ ስም ፡ በአስመራጭ ኮሚቴውና በመላው ሕዝበ ክርስቲያን ስም ደስታዬን እገልጣለሁ ።



ቅዱስነታቸው … የመጀመሪያውን ምዕዳንና ቃለ ቡራኬ ሲያስተላልፉ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ሆይ!

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ተጠባባቂ ሁኘ እንድሠራ ቅዱስ ሲኖዶስ ኃላፊነት ጥሎብኝ በእግዚአብሔር ቸርነት ምርጫው በትክክል ተከናውኖ ሢመቱ ከተፈጸመ ከአሁኑ ደቂቃ ጀምሮ መንበሩን እንዲረከቡኝ እለምናለሁ ።

ብፁዕ ወቅዱስ ሆይ!

በአሁኑ ጊዜ እንደ ቅዱስነትዎ ያለ ሠርቶ የሚያሠራ አባት ቤተ ክርስቲያናችን በማግኘቷ ከፍ ያለ ደስታ ታደርጋለች አሁንም ቅዱስ ሆይ የመጀመሪያውን ምዕዳንና ቅዱስ ቡራኬዎን እንዲያስተላልፉልን በሁሉም ስም እጠይቃለሁ በማለት ብፁዕ አቡነ አብርሃም ተጠባባቂው ሊቀ ጳጳስ ንግግራቸውን አጠቃለዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ። አዲሱን የሢመት ልብስ ለብሰው አክሊለ ክብራቸውን ተቀዳጅተው አርዌ ብርቱን ጨብጠው መንበረ ፓትርያርኩን ከተቀበሉ በኋላ የሚከተለውን ቃለ ቡራኬ አሰምተዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

## ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

"አኩት እግዚአብሔር በእንተ ፀጋሁ እንተ ኢትተረጎም ወትመጽእ አመ ኢተሐዝብዋ" ፪ኛ ቆሮ ፱፡፲፭ ስለማትመረመር ፡ ባላወቋት ዕለት ባልጠረጠሯት ሰዓት ስለምትሰጥ ፀጋው እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ።

ብፁዓን ሊቀ ጳጳሳት የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት!

ብፁዓን የልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ወኪሎች!
ክቡራን የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት ባለሥልጣኖች!
ክቡራን አምባሳደሮችና ኮር ዲፕሎማቲኮች!
የቤተ ክርስቲያናችን ካህናትና ምዕመናን!
የዚህችን ጥንታዊትና ባለታሪክ የሆነች ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን ሕይወት እንድመራ ፈቃዱ ለሆነና የእኔን ትሑት ሰብእና ላስመረጠ አምላክ ምስጋና አቀርባለሁ ፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተመሠረተ በቅዱሳን ሐዋርያት የተሰበከ በአበው ሊቃውንት የጸና ነው ።

የዚህም እምነት ትምህርት መነሻም ሆነ መድረሻ በኒቅያና በቁስጥንጥንያ ጉባኤዎች የተወሰነው ጸሎተ ሃይማኖት ነው የእኛም እምነት የተመሠረተውና የጸናው ለምእመናን የማስተምረው ፡ የምጠብቀውና የማስጠብቀው ይህንኑ ከሐዋርያት ሲያያዝ የመጣውን ፡ ሠለስቱ ምእት በኒቅያ ሠርተው ...ኑትንና ያጸኑትን ሃይማኖት ነው ።

ይህ መንፈሳዊ መዓረግ ከፍተኛ እንደመሆኑ መጠን ኃላፊነቱ ከባድ ነው ፡ ሆኖም የእግዚአብሔር ጸጋ በመሆኑ በክብር ስቀበለው ለማዕረጉ ያበቃኝ አምላክ አሁንም በቸርነቱ በቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ጸሎትና የሥራ ጥረት በመላው ካህናትና ምእመናን ኅብረት ሥራዬን እንደሚያቃናልኝ ኃላፊነቴንም በሚጠበቀው መልክ ለመወጣት እንደሚረዳኝ እምነቴ ጽኑዕ ነው ።

ሁሉንም ለአደረገና አሁንም ለማድረግ ችሎታ ለአለው አምላክ ከሁሉ አስቀድሜ ልባዊ ምስጋናን አቀርባለሁ እርሱ ያሰበውን የሚፈጽም ከሃሊ አምላክ ነው በሰብአዊ ሕሊና ሊገመት የማይቻለውን ከባድ ተአምራት ሁሉ የማድረግ ችሎታ ያለው አምላክ እርሱ ብቻ እንደመሆኑ የሁሉ ሠሪና መሪ ይሁን እንጂ ለሁሉ ታዛቢና ተቆጣጣሪ የሰውን ልጅ አድርጎታል ።

ለዚህም ዓለም መሥፈሪያና መለኪያ ያደረገለትን ያህል



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በመንበረ ክብራቸው እንደተቀመጡ



ደግሞ ያንን የሚቆጣጠሩ በቢያም መሠረት የሚመሩ ከሰው ወገን በየጊዜው እየመረጠ እያነግሠ እንደ ሀሳቡ ሲያደርግ የነበረ አምላክ ነው ፡ ዛሬም ያለው ወደፊትም ለዘለዓለሙ ጸንቶ የፈቀደውን ሁሉ ሲያደርግ የሚኖር እርሱ ብቻ ነው ፡ ቤተ ክርስቲያንንም የመሠረተ አምላክ ለቤተ ክርስቲያን ጠባቂዎችንና መሪዎችን የእርሱ እንደራሴዎች የሚሆኑትን በየጊዜው ሲያሥነሣ ቆይቷል አሁንም እኔ ይህን ቅዱስ ሥራና ከፍተኛ ኃላፊነት ስቀበል በእርሱ አጋዥነት የቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ተልዕኮ የተሟላ እንደሚሆን እምነቴ ጽኑዕ ነው ፡ በአሁኑ ጊዜ የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ተልእኮ ያሟላል ተብሎ የታመነበት የሰበካ ጉባኤ አቋም ነው ።

አሁንም እርሱን በበለጠ የማቋቋምና የማጠናከር ሥራ ቅድሚያ የሚሰጠው ይሆናል ቤተ ክርስቲያንም በዚህ አሠራር በበለጠ እንድትጠናከር ዛሬም ነገም የማስተላልፈው አደራ ይሆናል ቤተ ክርስቲያናችን የሥነ ጥበባት የዕውቀት ምንጭ ሁና እንደኖረች የታወቀ ነው ፡ ወደፊትም ይህ በበለጠ እንዲቀጥል ማድረግ የቤተ ክርስቲያናችን ተቀዳሚ ተግባር ይሆናል ፡ የቤተ ክርስቲያናችንን እምነትና ሥርዓት ለመጠበቅ ስብከተ ወንጌልን ማስፋፋትና የካህናት ማሠልጠኛ ማዕከሎችን ማጠናከር የቅዱስ ሲኖዶስ ቀዋሚ ተግባር እንደመሆኑ ይህ ተግባር እስከ አሁንም በቅዱስ ሲኖዶስ ትኩረት የተሰጠው ስለሆነ ወደፊትም በበለጠ የሚታሰብበትና ቅድሚያ የሚሰጠው ነው ።

ቤተ ክርስቲያን የነገውን ምእመን መተካት የምትችለው ዛሬ በሰንበት ት/ቤቶች አማካይነት በሚሰጠው ትምህርት ስለሆነ የሰንበት ት/ቤቶችን ማስፋፋትና ማጠናከር ወደፊትም ከቤተ ክርስቲያኒቱ ተቀዳሚዎች ተግባራት አንዱ ይሆናል ።

ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ አገልግሎት ብቻ ሳትወሰን ሕዝበ ክርስቲያኑ የሚገለገልበትንና አስፈላጊው ዕርዳታ የሚደረግበትን መሥራት አለባት ፡ ስለዚህም በቅርብም ሆኖ የችግሩ ተካፋይ



ቅዱስነታቸው ከልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት የተበረከተላቸውን የክብር ስጦታዎች ጥቂቶቹን በአንገታቸው አጥልቀው ይታያሉ

የምትሆንበት ከዚህ ቀደም የተለመደው የልማት ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይሆናል ፡ ለልማቱም ሥራ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጠዋል፡ እንዲሁም ስለሕዝብ ዕድገት ስለማኅበራዊ ኑሮ መቃናት ቤተ ክርስቲያናችን የምታበረክተው የተለመደ መንፈሳዊ አገልግሎት በስፋትና በጥራት እንዲካሔድ ይሆናል ፡ ቤተ ክርስቲያናችን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አባል ብቻ ሳትሆን ከመሥራቾች አባላትም ውስጥ አንደኛዋ ናት ።

ከዚህም ጊዜ ጀምሮ በበኩሏ ብዙ አስተዋጽኦ ስታበረክት ቆይታለች ወደፊትም ይህን የውጭ ግንኙነቷን በማጠናከር የበለጠ ዓለም አቀፍ አገልግሎት ለማበርከት ጥረት ታደርጋለች ፡ ሰላም በሀገራችን ሰላም በመላው ዓለም ይሰፍን ዘንድ የዘወትር ጸሎታችን ብቻ ሳይሆን ስለሰላም እንናገራለን ስለ ሰላም እንሠራለን በዓለም ላይ ሰላም የተጠበቀ እንዲሆን የየግሉ ሰላም ይጠበቃል ይኸውም ከሆነ ሁሉ የሚደክምበትን የሥራ ውጤት ያገኛል ስለዚህም አሁንም ቤተ ክርስቲያን ሁሉን ወደ ሰላም ትጠራለች ስለሰላምም ትጸልያለች ።

ቤተ ክርስቲያናችን ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን እንደመሆኗ ሕዝቡ ሕዝባችን ነው ፡ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ጐን ተሰልፋ ስለ ሕዝብ አንድነት ስለ ዕውቀት ፡ ስለማኅበራዊ ኑሮ መቃናት ፡ ስለሰው እኩልነት ስለ ትክክለኛ ፍትሕ ልትሠራና ልታስተምር ይገባታል ፡ ይህንንም ሁሉ በመገንዘብ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያንን ሁሉ ስታገለግልና ስታስተምር ኑራለች ወደፊትም በተጠናከረ ሁኔታ ትቀጥላለች ፡ የሰላምና የአንድነት ጥሪንም ታስተላልፋለች ።

የልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ወኪሎች ዛሬ በዚህ በዓል ላይ በመገኘታችሁ የነበረውንና ያለውን ግንኙነታችን በበለጠ ስለሚያጠናክር በቤተ ክርስቲያናችን ስም እናመሰግናለን ፡ በዚህ በዓል ለመገኘት ጥሪያችን አክበራችሁ የመጣችሁ ክቡራን አምባሳደሮች ለሁላችሁም በቤተ ክርስቲያን ስም ምስ



www.ethiopianorthodox.org

ጋና እናቀርባለን ።

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያር ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ዕረፍት ጊዜም እንዲሁ ተግኝታችሁ ኀዘናችሁን መግለጣችሁን እናስታውሳለን ፤ ዛሬም እንዲሁ በመገኘታችሁ ስለ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ፍቅር ያላችሁ መሆኑን ያሳያል ስለዚህ ከፍ ያለ ምስጋና እናቀርባለን ።

ስለዚህ እናንተንም እግዚአብሔር ያክብራችሁ እኔም እናንተም ለቆምንበት ዓለማ የየድርሻችንን አበርክተን ከሊቀ ካህናት ከኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ቀርበን "አገብር ኄር ወምእመን ዘበውሁድ ምእመነ ኮንከ ባዕ ውስተ ፍሥሐሁ ለእግዚእከ" አንተ ታማኝ አገልጋይ በጥቂት የታመንክ በብዙ እሾምሃለሁ ወደጌታህ ደስታ ግባ የሚለውን አምላካዊ ድምፅ በመስማት ምስጋና ለማግኘትም የምንበቃ ያድርገን ።

የእግዚአብሔር አብ ጸጋ የእግዚአብሔር ወልድ ። ቸርነት የእግዚአብደሔር መንፈስ ቅዱስም አንድነት ከሁላችን ጋር ይሁን በማለት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ቃለ ቡራኬያቸውን ፈጽመዋል ።

የቅዱስነታቸው ቃለ ቡራኬ እንደተፈጸመ

"መሐለ እግዚአብሔር ወኢይኔስሕ አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ እግዚአብሔር በየማንከ የሚለው መዝሙረ ዳዊት ተሰብኮ ቅዱስነታቸው ከዮሐንስ ወንጌል ፲፩—፲፰ አንብበው ጸሎተ ቅዳሴውን በመምራት የቅዳሴው ጸሎት ካበቃ በኋላ ፬ ሰዓት ተኩል ሲሆን ቅዱስነታቸው በብፁዓን ሊቃ ጳጳሳት ግራና ቀኝ በመታጀብ ከቅድስተ ቅዱሳኑ ወደ ዓውደ ምሕረቱ ሲወጡ በዚያ የተሰበሰበው ሕዝብ ደስታውን በመዝሙር በጭበጨባና በልልታ ገልጿል ።

ቅዱስነታቸው በተዘጋጀላቸው መንበረ ክብር እንደተቀመጡ ከአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት የተወጣጡ ጥንግ ድርብ የለበሱ መዘምራን "ይቤሎ ጳውሎስ ለመርቆሬዎስ የሚለውን ያሬዳዊ ዜማ አለዝበው ለ፴ ደቂቃ አሸበሸቡ የሰንበት ተማሮችም መንፈሳዊ መዝሙር ዘምረው ሲያበቁ የተፈቀደላቸው ፫ ሊቃውንት ቅኔ አበርክተዋል ።

ቀጥሎም የውጭ ሀገር አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች ከሕንድ ከአርመን ከግሪክ ከቁስጥንጥንያ ከራሺያ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የካንትርበሪው ሊቀ ጳጳስ እንዲሁም ከሮማው ፓፓ ሁለተኛ ጳውሎስ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ከሎተሪውያን ከመካነ ኢየሱስ የተላኩ መልእክቶች በመልእክተኞቹ ተነበው ከየአብያተ ክርስቲያናቱ የተላኩ ከፍተኛ የሆኑ ስጦታዎችም ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእስ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ተበርክተዋል ።

በሥነ ሥርዓቱም ላይ ጓድ ዶ ር ዲበኩሉ ዘውዴ የሃይማኖት ሚኒስትር አምባሳደሮች ተገኝተዋል ።

የየአብያተ ክርስቲያናቱ ተወካዮችም የተሰማቸውን ደስታ ገልጸዋል ከአብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች መካከል የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ተወካይ ፕሮፌሰር ብርያ ያደረጉት ንግግር።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ብፁዕ ወቅዱስ ሆይ !

ዶክተር ሚሚሊዮ ካስትሮ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ዋና ጸሐፊ ሰም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሁነው በመመረጥዎና በመሾምዎ እንኳን ደስ አለዎ ስል ከፍ ያለ ክብር ይሰማኛል በዚህ ታላቅ በዓል ላይ እንድንገኝ በመጋበዛችን እጅግ ደስ ብሎናል ።

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር በዚህ በዓለ ሢመት የተደሰተባቸው ሁለት ምክንያቶች አሉት አንደኛው በአለፈው ወር የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር በአመስተርዳም የዛሬ ፵ ዓመት የተመሠረተበትን የመታሰቢያ በዓል በአከበረበት ጊዜ ለቤተ ክርስቲያኗ ታላቅ ምስጋና ቀርቧል ይህም የሆነበት ምክንያት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከመሥራች አባላት አንዷ ስለነበረች ነው ፤ በእነዚህ ፵ ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በየጉባኤው ጳጳሳትን የቴክኖሎጅ ሊቃወንትን ካህናትን ምእመናንን በመወከሏ በማኅበር ከፍተኛ አስተዋጽኦን ስትሰጥ ቆይታለች በዚህ መንገድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከክርስትናው ዓለም ውስጥ አፍሪካን በመወከል ታላቅ ሚናን ተጫውታለች ።

ሁለተኛ በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ክርስቲያንም በዓለም አቀፍ እንቅስቃሴ ውስጥ ለፍትሕ ፤ ለሰላምና ለእድገት ለሚደገረም ጥረት ተካፍይ መሆኗ በጋራ ለምንሠራው ሥራ ምስክርነት መስጠት ሲሆን ይህም የሚጠቅመው አፍሪካን ብቻ ሳይሆን መላውን ዓለም ነው።

በዓልም አቀፋዊ አንድነታችን ሕዝብዎ ተቸግሮበት በነበር ጊዜ በጋራ መልስ ለመስጠት ተሞክሮ አለ ፤ በዓለም ላይ ብዙ ሰዎች ሰላምን ፍትሕን ፤ ነፃነትን ይሻሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የመንፈሳዊ ሕይወት መድበል ስለሆነች የዓለም ኅብረተሰብ ከእርሷ ብዙ የሚማረው ነገር አለ ።

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የኢትዮጳያን ሕዝብ ዕድገትና ብልጽግና ይሻል እንደርስዎ ያለች ለታሪክ ቤተ ክርስቲያን የሕዝብን መሻሻልና ተሐድሶ በብርቱ እንደምትመኝ እሙን ነው በታሪካዊ አመጣጧ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሕዝቡ ጋር የጠበቀ ቃል ኪዳን አላት ። እምነቷም ከሐዋርያትና ከአበው ሊቃውንት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ በመሆኑ ለሕዝቡ የምትሰጠው ምስክርነት ተጨባጭ ነው።

እንደዚህ ያለች ቤተ ክርስቲያን ጠንካራ መሪ ያስፈልጋታል ፤ የፓትርያርክነት ዘመንዎ የተባረከ እንዲሆንልዎ እንመኛለን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያላትን መንፈሳዊ ጥበብ ለዓለም ኅብረተሰብ እንደምታካፍል ተስፋ አለን ፤ በጋራ ባለን እምነት መነሻ እግዚአብሔር ለአዲሱ ፓትርያርክ ፤ ለቅዱስ ሲኖዶስ ፤ ለካህናትና ምእመናን ጽንዓቱንና ብርታቱን እንዲሰጥልን እንለምናልን መንፈስ ቅዱስ ለቅዱስነትዎም ብርታቱንና ጽንዓቱን እንዲሰጥዎ እንለምናል ፤ የኢትዮጵያንም ሕዝብ እንዲባርክ እንጸልያለን በማለት ፕሮፌሰር አይወን ብርያ የተሐድሶና የማኅበረ ምእመናን ድሬክተር ንግግራቸውን አጠቃለዋል ቀጥሎም ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ የሚከተውን ንግግር አድርገዋል ።

## የብፁዕነታቸው ንግግር

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ብፁዕ ወቅዱስ ሆይ!

ቤተ ክርስቲያናችን እንደቀደምት አብያተ ክርስቲያናት ክብርን ከተጐናጸፈች ብዙ ዘመናት አልፈዋል ፤ ይኸውም አበው ሲያልፉ አበውን በመተካት ከአባት ወደ አባት በመተላለፍ ነው ፤ ኀዘንም ሆነ ደስታ የሚፈጸመው በጎረቤት በዘመድና በወዳጅ ጭምር እንጂ በባለቤት ብቻ አይፈጸምም እኛም በዚህ ወቅት ከጎረቤቶቻችን ከወዳጆቻችን የተላኩልንን የኀዘን መግለጫዎች አንበናል ዕምተናልም በእነርሱም ከኀዘናችን ተጽናንተናል ።

በመንግሥትም በኩል ሙሉ ትብብርና ድጋፍ ተደርጎልናል ስለዚህም በዚህ አጋጣሚ ምስጋና እናቀርባለን በዚህ በያዝነው ዓመት በግንቦት ወር ከ ፳፱ ቀን እስከ ነሐሴ ፳፱ ቀን ፲፱፻፹ ዓ·ም· ድረስ እግዚአብሔር የወሰናቸውና ያቀዳቸው በሰው ልጅ ዘንድ ግን ያልታሰቡና ያልተጠረጠሩ ሁለት ታላላቅ ድርጊቶች በቤተ ክርሲቲያናችን ተፈጽመዋል ። ይኸውም የነበሩንን ቅዱስ አባት በማጣት በምትክም ቅዱስነትዎን ማግኘት ነው ።

የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ አካል የሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ የተለየበትን ቅዱስ አባት በሕመማቸው ወቅት ጸሎተ ምህላ ለሰባት ቀናት በመያዝ በተኙበት አካባቢ ባለመለየት በዕረፍታቸውም ጊዜ በዝማሬ ካህናትና በማኅሌት በመሸኘትና የኀዘኑን ዕለታትም በአንድነት በጸሎትና እንግዶችን በመቀበል አክብሮ ከፈጸመ በኋላ ባለበት ኃላፊነት ሕያዊትና ዘለዓለማዊት ለሆነችው ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበር ተተኪ አባት ለማግኘት የአንድነት ጸሎቱን ቀጠለ በዚህም መሠረት በቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት የምርጫ ደንብ አውጥቶ አስመራጭ ኮሚቴ ወይም የምርጫው ሥራ እንዲካሄድ ውሳኔ አሳለፈ ።

ባሳለፈውም ውሳኔ መሠረት ኮሚቴው የተጣለበትን መንፈሳዊ አደራ ለመወጣት ባደረገው ያልተቆጠበ ጥረት በቅዱስ ሲኖዶስ የበላይ አካልነት በኮሚቴው ተጠሪነት በካህናትና በምእመናን ተጠሪዎች መራጭነት ነሐሴ ፳፱ ቀን ፲፱፻፹ ዓ/ም የተከናወነው የምርጫ ውጤት ቅዱስነታዎን ለቤተ ክርስቲያናችን ተተኪ አባት አድርጎ ስላስገኘልን ደስታችን ፍጹም ነው ቀደም ሲል በኀዘናችን ወቅት ከወዳጆቻችን በተላከልን የኀዘን ማጽናኛ እንደተጽናናን እነሆ ዛሬ ደግሞ በሰጡት መግለጫቸው ደስ ብሎናል ፤ ይልቁንም ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ሀገር ወዳጆቻችን ሁሉ በመምጣትና በበዓላችን ላይ በመገኘት የደስታችን ተካፋዮች በመሆናቸው ደስታችን የላቀ ነው ።

ብፁዕ ወቅዱስ ሆይ

አሁንም ልዑል እግዚአብሔር ለቅዱስነትዎ ዕድሜና ጤንነትን ለዓለም ሁሉ ሰላምን ፤ ለቤተ





www.ethiopianorthodox.org

# እናቱና ክርስቶስ በምን ምክንያት ተሰደዱ

የስደት ዓይነቱ ስንት ነው ? ስደት መቼ በማን ተጀመረ ? እኒህን እና እነዚህን የመሣሠሉትን በቅደም ተከተል እናቀርባለን።

የስደቱ ዓይነት ስንት ነው ? ለተባለው ዋና ዋናዎቹ ሶስት ሲሆኑ እነርሱም ፡

ሀ/ ድርቅ እና ረኃብ ፡

ለ/ ፖለቲካ ፡

ሐ/ ጦርነት ናቸው ስደት መቼ በማን ተጀመረ ? ለሚለው የኅብረተሰቡን ኑሮ እና አጀማመር ያጠኑ ሊቃውንት ሰው በማሕበራዊ ኑሮ መኖር ከጀመረበት ጀምሮ ነው ሲሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ደግሞ አራት ዘፍጥረት ፲ ይተርካሉ ። ታሪኩም ባጭሩ እንደሚከተለው ይነበባል ። በከነአን ለሦስት ዓመት ያህል ዝናም ስላል ዘነበ ድርቅ ሆነ በድርቁም ምክንያት ረሀብ ስለፀና አባታችን ያዕቆብ ሰባ አምስት (፸፭ ቤተሰቡን ይዞ በዓባይ ውሃ ወደምትጠቀመው ወደ ግብፅ ተሰደደ ስደተኛም ሆኖ ከኖረ በኋላ በዚያው ሞተ ልጆቹም ሆኑ የልጅ ልጆቹ በግብጽ ለአራት መቶ ሠላሣ (፬፻፴) ዘመን ያህል በባርነት ቀንበር ተይዘው በስደት ኖሩ የፖለቲካ ስደት ደግሞ በሀፃኑ ኢየሱስና በድንግል ማርያም ላይ እንደተከሠተ ወንጌላዊው ማቴዎስ የጻፈውን እንመለከታለን ።

"እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ለዮሴፍ ታየው ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልጋዋል ፡ እና ከእንቅልፍህ ተነሣና ሕፃኑን እና እናቱንም ይዘህ ወደ ግብፅ ሽሽ ተመለስ ብዬ እስከነግርህ ድረስ በዚያው ተቀመጥ አለው" ዮሴፍም እንዳዘዘው አደረገ ከዚያ በኋላ ሄሮድስ ሕፃኑን ክርስቶስን ያገኘ ስለመሰለው በሰባ ሰገል አቆጣጠር በተረዳው ዘመን ሹማምንቱን ልኮ በቤተ ልሔም እና በአውራጃዋ የነበሩትን ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት ዕድሜ ያላቸውንና በብዙ ሺህ የሚቆጠሩትን የባሬ አበባ የነገ ፍሬ የሆነው አገሪቱን የሚረከቡትን ሕፃናት አስፈጃቸው ።

ሕፃኑ ኢየሱስ ግን በጉዞ ላይ ስለነበር ሊያገኘው ባለመቻሉ ሐሳቡ አልተሳካለትም ። የሕፃኑ ኢየሱስና የድንግል ማርያም የስደት ጉዞ እንደሚከተለው ይቀርባል ።

ድንግል ማርያምና ሕፃኑ ኢየሱስ ወደ ግብፅ የተሰደዱት በረኃብ ወይም በድርቅ ምክንያት ሳይሆን በፖለቲካ ነበር ። ይኸውም ንጉሥ ሄሮድስ መንግሥቱን ይወርሳል ብሎ ሕፃኑ ኢየሱስን ሊያስገድለው ስለፈለገ ነው እነማማቸውም ከቤተ ልሔም ሲሆን በኬብሮን አድርገው ለኪሶንን ወደ ግራ እየተው ቤርሳቤህን እየተከተሉ ሰርጥ ሰርጥ መንገድ እየፈለጉ እስከነጋዴዎች መንገድ ድረስ ተጉዘዋል ከዚያም ሲደርሱ ነጋዴዎችን መንጠቅ የለመዱ ሽፍቶች የያዙትን ዕቃ ነጠቁአቸው የነጠቁአቸውም በዚያን ሰሞን ነጋዴዎች ቀርተው ስለነበር ሽፍቶቹ የገንዘብ ችግር ደርሶባቸው ስለነበር ነው ። ይባላል በኋላ ግን የወሰዱባቸውን ዕቃ መልሰውላቸዋል እመቤታችን እና ዮሴፍም የተጓዙት በሀገር ውስጥ መንገድ ነበር በዚህም መንገድ ተጉዘው ወደ ግብጽ ገብተዋል ወደ ግብፅም የተሰደዱበት ዋናው ምክንያት አገራቸው የሮማውያን ቅኝ ግዛት ስለነበረች እስራኤላውያን ይሰደዱ የነበሩት ወደ ግብፅ ስለነበር እመቤታችንም የተሰደደችው በዚህ ምክንያት ነው ። በዚህ ዘመን አንድ ሚሊዮን የአይሁድ የፖለቲካ ስደተኞች በግብፅ ይኖሩ እንደነበር ከታሪክ ለመረዳት ይቻላል ኢሳይያስም ክርስቶስ ወደ ግብፅ እንደሚሄድ በትንቢት ተናግሮ ነበር ። ኢሳይያስ ም ፲፱ ቁ ፩ ሆሴም ልጄን ወደ ግብፅ ጠራሁት ይላል ም·፲፩·ቁ ፩ ይህም ትንቢት ተፈጽሞ ሕፃኑ ኢየሱስና ቅድስት ድንግል ማርያም ከዮሴፍና ከሰሎሚ ጋር ሦስት ዓመት ከመንፈቅ የፖለቲካ ስደተኞች ሆነው በግብፅ ተቀምጠዋል ። አያሌ መከራና ግፍም ተፈጽሞባቸዋል ። ሄሮድስ ለምን አሳደዳቸው የሚል ጥያቄ ቢቀርብ ሰባ ሰገል የምሥራቅ ጠቢባን በቤተ ልሔም ንጉሥ ተወልዷል ወርቅ ፡ እጣን ፡ ከርቤ ፡ ልንገብርለት መጥተናል ብለው ለሄሮድስ ስለነገሩት መንግሥቱን ይወርሣል ብሎ በመፍራት ነበር ። ያን ጊዜ ፍልስጥኤም የሮማውያን ቅኝ ግዛት ስለነበረች ሄሮድስ ስለ ሀገሩ ነፃነትና መብት ከሮማውያን ጋር መዋጋት ሲገባው እንደዬት ለሀገሩ ጠላቶች ሎሌ እና ባንዳ ሆኑ የስም ዘውድ ደፍቶ የፍልስጥኤም ንጉሥ ነኝ ብሎ ሰማያዊ እንጂ ምድራዊ ገገር ያል ሆነውን ሊገድለውና ሊያስገድለው ፈለገ እውነትም የጠላት አሽከር መሆኑን ሥራው ያረጋግጣል። ይህ ከሆነ የእሱን ታሪክ እንመልከት ።

ታላቁ ሄሮድስ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ፴፯ ዓመተ ዓለም እስከ ፬ ዓመተ ዓለም በንጉሥነት ኖሯል በትውልዱ ኤዶማዊ ሲሆን የኤማው ዘር መሆኑ በታሪክ ተገልጿል ።

የይሁዳን መንግሥት ለመያዝ ምክንያት እንደሆነው ሂርቃኖስ የተባለውን የአይሁድን መሪ ገድሎ ማሪያሚን የተባለችውን ልጁን አገባ ከእርስዋም ሁለት ወንድ ልጆችን ወለደ ። መጀመሪያ አጎቷን ገደለ ሚስቱንም በትናት ከገደለ በኋላ ከእርስዋ የወለዳቸውን ሁለት ልጆች የሰው ወሬ በመስማት በሰይፍ አስመታቸው ይኸው ሄሮድስ ፩፻ በኮከብ እየተመሩ የመጡትን ሰብአ ሰገል ያነጋገረ ፡ ፪ኛ እመቤታችንን ከሕፃኑ ኢየሱስ ጋር እንዲሰደዱ ያደረገ ፡ ፫ኛ በሕፃኑ በኢየሱስ ምክንያት የቤተ ልሔምን ህፃናት ያስፈጀ በዚሁም የከፋት ሥራው አረማዊ ሄሮድስ ተብሎ የጠራው ነው ።

ይኸው ሄሮድስ ድንገል ማርያምን እና ሕፃኑን እየሱስን ካሣደደና ሕፃናትን ካስገደለ በኋላ በሕዝቡ በኩል ሁከት እየተፈጠረ ፀጥታ ከመጥፋቱም በቀር እራሱም ሰላምና ጤንነት አጥቶ ከመታወኩም ሌላ በቁስል በሽታ ተይዞ ይሠቃይ ጀመር ።

ጆሴፍስ የተባለው የአይሁድ ታሪክ ፀሐይ ስለ ሄሮድስ የቁስል በሽታ እና አሟሟት ሲጽፍ በመጀመሪያ ጊዜ ሰውነቱ ስለቆሰለ በአዋቂዎች መድኃኒት ይጠቀም ጀመር መድኃኒቱም ስላላዳነው በጥብርያዶስ ባህር አጠገብ ከሚገኘው ፍል ውሃ ገብቶ ለብዙ ቀን ታጠበ በእርሱም ፈውስ ሊያገኝ አልቻለም ቀጥሎም በዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ ከሚገኘው በገለአድ ውስጥ ካለው ሞቃት ለብዙ ቀን በእንፋሎቱ ተነከረ ከዚያም ደኅንነትን ባለማግኘቱ በኢያሪኮ ባሻገር ለእናቱ ባሰራው ቤተ መንግሥት ተኝቶ ይታመም ጀመር ።

በመጨረሻም እህቱ ሰሎሚንና ታማኝ አሽከሮቹን ጠርቶ የሚከተለውን ኑዛዜ ተናዘዘ እንግዲህ እድናለሁ ብዬ ብዙ ቀን ለፋሁ አልሆነልኝም መሞቴ ነውና መሳፍንቱን እና መኳንንቱን እንዲሁም ምስለኔዎችን ይዛችሁ እሠሩዋቸው እኔ ስሞትም ግደሉዋቸው ይህንንም የምታደርጉት እኔን ሕዝቡ ስለጠላኝና ስለማያለቅስልኝ በእነሡ ምክንያት እንዲለቀስልኝ ሲል ተናዘዘ ታናሽ እህቱ ሰሎሚም እሱ ወዲያው እንደሞተ ኑዛዜውን ለውጣ ይፈቱ ሲል ተናዟል ስትል እንዲፈቱ ተናገረች ባይለቀስለትም በክብር ተቀበረ ።

ሞት አይቀርምና ተንገላቶና ብዙ ተሰቃይቶ ሄሮድስ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ ። በዚህ ጊዜ ሕፃኑ ኢየሱስና እናቱ ድንግል ማርያም ሰሎሚና ዮሴፍ ጭምር ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ግብፅ በስደት ከቆዩ በኋላ ሄሮድስ በመሞቱ "እነሆ የጌታ መልአክ በግብፅ ለዮሴፍ በሕልም ታይቶ የሕፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና ተነሣ ሕፃኑን እና እናቱን ይዘህ ወደ እስራኤል ሂድ አለው እርሱም ተነሥቶ ሕፃኑን እና እናቱን ያዘና ወደ እስራኤል አገር ገባ በአባቱም በሄሮድስ ፋንታ አርኬላዎስ በይሁዳ እንደነገሠ በሰማ ጊዜ ወደዚያ መሄድን ፈራ ይኸውም ሄሮድስ አርኬላዎስ ደግሞ እንደ አባቱ ጨካኝና ክፉ ስለነበር ክርስቶስ ወደ ቤተ ለሔም እንዳይመጣ ወደ ናዝሬት እንዲሄድ መላኩ ለማርያም የነገራት እንዳይገድለው በማለት ነው ።

እንግዲህ በእመቤታችን በድንግል ማርያም ብዙ ግፍ እንደተፈፀመባት በመጀመሪያው ርእስ እንደጻፍን ይታወሳል ለምሳሌ አንድ ሰው አንዳች በደል ሳይሠራና ሳያጠፋ ሳይፈርድበት ከንብረቱ ከቤቱ ወጥቶ ከወገኑ ከዘመድ ተለይቶ እንዲሄድና ከሚወደው አገሩ ወጥቶ እንዲሰደድ ቢደረግ መብቱን እና ነፃነቱን መድፈር ብቻ ሳይሆን ከዚህ የበለጠ መከራና ግፍ የለም በእመቤታችንም በድንግል ማርያም የተፈፀመው ግፍና ስቃይ ከዚህ ይበልጣል እንጂ አያንስም አንድ ባለቅኔ እንደተናገረው የእመቤታችን መከራዎቿ አራት ናቸው ብሏል እነዚህም ፡

፩ የሌሊት ቁርና ሀሩር

፪ መንገዱን ትታ በሰርጥ ስለምትጓዝ ቁልቁለቱን በመውረድ ሽቅበቱን በመውጣት እሾሁና እንቅፋቱ ፡ የበረሃው ጉዞና ድካሙ ።

---

ክርስቲያኖችን አንድነትን እንዲስጥልን በራሴና በቅዱስ ሲኖዶስ እንዲሁም በካህናትና በምእመናን ስም ምኞቴን እየገለጽኩ በዚህ ታሪካዊና ታላቅ በዓል ላይ ለተገኙ የበዓሉ ተካፋዮች ዕንግዶችና ሕዝበ ክርስቲያን ቅዱስ ቡራኬዎን እንዲያስተላልፉልን በትሕትና እጠይቃለሁ ፡ በክርስቶስ ሰላም ኢትዮጵያ ትቅደም በማለት ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ ንግግራቸውን ፈጽመዋል ።

ቀጥሎም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ጸሎተ ቡራኬ አድርገው የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል ።

የዜናው አቅራቢ
ሊቀ ትጉሃን ወርቅ





www.ethiopianorthodox.org

፫/ ረሀብና መጠማት ነው

፬/ ልጇን በራበውና ውሃ በጠማው ቁጥር እየተዘዋወረች በየመንደሩ ስትለምን እንደ እሳት የሚገርፈው የሰው ፊት አንድ ነው ብሏል ።

ይህን ሁሉ ችላና ታግሣ ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ያህል ተቸገረች ተንከራተተች ።

ስለዚህ አባ ሕርያቆስ በድርሰቱ ድንግል ሆይ እርጉም በሆነው በሄሮድስ ዘመን ከልጅሽ ከክርስቶስ ጋር ከአገር ወደ ሀገር ስትሸሺ ከአንቺ ጋር መሰደዱን አሳስቢ ፤ ድንግል ሆይ ከዓይኖችሽ የፈሰሰውን እና በተወደደ ልጅሽ ፊት የወረደውን መሪር እንባ አሳስቢ ረሐቡንና ጥሙን ፤ ችግሩንና ሐዘኑን ከእርሱ ጋር የደረሰብሽንም ጭንቅ ሁሉ አሳስቢ ብሏል ቅዳሴ ማርያም ቁጥር ፩፻፳፯—፩፻፳፱ ሊቁ እንዳለው በእመቤታችን በድንግል ማርያምና በሕፃኑ በእየሱስ ላይ የደረሰውን ግፍና መከራ ተመልክተናል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ይህን መሠረት በማድረግ በየዓመቱ ከመስከረም ፳፮ እስከ ኅዳር ፮ ቀን ድረስ ለ፵፱ ቀናት ዘወትር በጸሎትና በኀዘን በየሳምንቱ እሁድ በማህሌት በቅዳሴ የደረሰባትን ስደትና ግፍ ወርሃ ጽጌ በሚል ስም እየጠራች ታስታውሳለች ምእመናኑም የጸሎትና የቅዳሴው የኀዘኑና የሰቆቃው ተካፋይ እየሆኑ ስደቷን ያስተውሳሉ ።

በልጇና በእርሷ ስደት ሕይወት አግኝተዋልና የእመቤታችን ስደት ይህንን ሲመስል የስደት መነሻው ግን ብዙ ነው ይኸውም ፖለቲካ ግጭት የሃይማኖት የተዋር እጦት ማለትም ድርቅና ረሃብ ፤ የመሬት መንቀጥቀጥ በሚያደርሡት የሚመጣ ስደት ፤ እርስ በእርስ በመዋጋት የሚመጣ የጦርነት ስደት ይህም በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ በአፍሪካ ፸ ሚሊዮን ስደተኞች ይገኛሉ እነዚህ በተባበሩት መንግሥታትና በልዩ ልዩ ድርጅት የሚረዱ ናቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ከዓለም አብያተ ክርስቲያናትና ከተባበሩት መንግሥታት ጋር ተራድኦ ለማድረግ ስምምነት እንዳደረገች ይታወቃል ።

ይኸውም ቤተ ክርስቲያናችን በመላው ዓለም ስለሚኖሩ የሰው ልጆች ሰላምና ደህንነት ዘወትር ወደ እግዚአብሔር ከምታቀርበው አጠቃላይ ጸሎትና ልመና የስደተኞችና የምርኮኞች ማዕናት ጭምር ይገኝበታል በጸሎትና በቅዳሴ ጊዜ በማሰብና ወደ እግዚአብሔር በማሳሰብ ብቻም ሳይሆን ቤተ ክርስቲያናችን ዘመን ለከፋባቸውና ወራት ለባሰባቸው ወገኖች ሁሉ መጠጊያና መጠለያ በመሆን ሰብአዊ አገልግሎት ስታቀርብ ኖራለች ይልቁንም ባለንበት ዘመን በተለያዩ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች በዓለም ሕብረተሰብ ኑሮ የሚደርሱትን ችግሮች ለመከላከልና ለመቋቋም የአብያተ ክርስቲያናትና የሰላም አፍቃሪ ክፍሎች ሐላፊነት እየበዛና እየከበደ በመምጣቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤትና ከመላው አብያተ ክርስቲያናት አጠቃላይ ጉባኤ ጋር ባደረገችው ስምምነት በኢትዮጵያ የሚገኙ ስደተኞችን ጉዳይ በሐላፊነት ተቀብላ ስታገለግል ዓመታት አልፈዋል ። ይህም ሲደረግ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ የተቋቋመ የስደተኞች ጽሕፈት ቤት አለ በዚህ መሥሪያ ቤት ይህን ለማስፈጸም ቤተ ክርስቲያናችን ከላይ እንደ ተገለፀው ከዓለም አብያተ ክርስቲያናትና ከተባበሩት መንግሥታት ጋር በጋራ በአደረገችው ስምምነት ምግብና መጠለያ በመስጠት ከአንደኛ ደረጃ እስከ ዩንቨርስቲ ደረጃ በማስተማርና በልዩ ልዩ ሙያዎች በማሠልጠን ከ፪ሺህ፳፯ በላይ ስደተኞችን ትረዳለች ።

እነዚህም ስደተኞች ከቺኮዝላቫኪያ ፤ ከሱዳን ፤ ከሶማሊያ ፤ ከኬንያ ፤ ከኡጋንዳ ፤ ከዛየር ፤ ከደቡብ አፍሪካ ፤ ከናሚቢያ ፤ ከሩዋንዳ የመጡ ናቸው ።

ሁላችንም የስደትን አነሣሥና አመጣጥ ተመልክተናል ነገ በእኔ ነው እና ስደተኞችን ባለን አቅም እንርዳ ።

አለቃ ነቢየልሁል ዮሐንስ

# ደብዳቤዎች

(ከገጽ ፩ የዞረ)

ቄው እንዳሳሰቡት እኛ የምናስተላልፈው መንፈሳዊ መልእክት አማኒ የሆነ ሁሉ የሠራውን ኃጢያት እየተናዘዘ ሥጋውንና ደሙን እንዲቀበል ነው ሰባክያነ ወንጌልም እንደመጥምቁ ዮሐንስ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያሉ ከማስተማር ወደ ኋላ እንዳይሉና ያለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ዘለዓለማዊ ድኅነት እንደሌለ በትጋት ያለማቋረጥ እንዲያስተምሩ መንፈሳዊ መልእክታችን በማስተላለፍ መልሳችንን እናጠቃልላለን ።

# የምሥራች

ከሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ

የክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣት የሰውን ልጅ ድኅነት የሚያበሥር በመሆኑ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ያስተማረው ትምህርት ወንጌል ይባላል ፤ የምሥራች ማለት ነው ። በሰው ልጅ ላይ ሠልጥኖ የነበረው ሞተ ሥጋም ሞተ ነፍስም እንደጠፋ ፤ ዲያብሎስ እንደተሻረ የሰው ወገን ሁሉ በክርስቶስ ነፃ እንደወጣ ይናገራልና ። ይኸን ወንጌል የጻፉ ያስተማሩ ወንጌላውያን ይባላሉ የምሥራች ተናጋሪዎች ማለት ነውና ።

በሰፊው አነጋገር ደግሞ ፳፯ቱ የሐዲሳት መጻሕፍት ሁሉ ወንጌላት ይባላሉ ፤ ምክንያቱም ሁሉም ይኸነኑ አንዱን ዓይነት የምሥራች ይናገራሉና ። በጠባብ አነጋገር ግን ወንጌላት የሚባሉት ፬ቱ መጻፍት በቅ·ማቴዎስ ፤ በቅ·ማርቆስ ፤ በቅ·ሉቃስ በቅ·ዮሐንስ የተጻፉ ብቻ ናቸው ። እነዚህ ፬ቱ ወንጌላት ለሌላው የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ሁሉ መነሻ የሆኑ የምሥራቹ ትክክለኛ መግለጫ ናቸው ፤ በነዚህ ወንጌላት ጨለማው ዓለም በርቷል ፤ የራቀው ሕዝብ ቀርቧል፡ በነዚህ መጻሕፍት ባዕዱ ዘመድ ሁኗል ።

ክርስቶስ የተናገረው የምሥራች ፤ ያስተማረው ትምህርት ሁሉ በነዚህ ወንጌሎች የተገለጠ ነው ፤ እነዚህ ወንጌሎች ለክርስትናው ትምህርታችን መነሻ እንደ መሆናቸው ገና በክርስቶስ ያላመነው ሕዝብ ይኸን ሰምቶ እንዲያምን የሚረዱ ናቸው ። በክርስቶስ ያመኑት ተስፋቸው አለኝታቸው ክርስቶስ የሆነ በእርሱ አምነው በትምህርቱ ጸንተው እንዲኖሩ የሚያደርጉ እነዚህ ወንጌሎች ናቸው ።

ወንጌል ክርስቲያኑን ወገን ለማብዛት ከፍተኛ መሣሪያ የሆነውን ያህል ክርስቲያኑን ደግሞ ባለበት ለመጠበቅ ወንጌል የበለጠ ኃይል አለው ።

እንግዲህ ከክርስትና ውጭ የሆነውም ክርስቲያኑም ሕዝብ ስለእርሱ የሚነገረውን የምሥራች ተስፋ መስማት ያስፈልገዋል ስለዚህ ወንጌልን ማንበብ አለበት በእምነቱ ጽናትን ያገኝ ዘንድ እሁንም ወንጌልን ማንበብ ያስፈልገዋል ። እንግዲህ በብዙ አቅጣጫ የሚጠቅመውን የወንጌልን ጥናት ማንም ቸል ሊል አይገባውም ፤ ወንጌልን በጸሎት መልክ በየጊዜው መመልከት መጸለይ ያስፈልጋል ። እንዲሁም በጥናት መልክ ወንጌልን በየጊዜው ማንበብ በወንጌል መመሪያነት መጽናት አለበት ።

ወንጌልን ግልጥ ለማድረግ ወደ አማርኛ ከመተርጐማችን ጋር እነሆ በሐተታ በትንተና ዘርዝረን ትርጉሙን እናቀርበዋለን ፤ እርሱንም እንደሚከተለው እናቀርባለን።

# የማቴዎስ ወንጌል ትርጉም

መቅድም፡—

የመጀመሪያው ወንጌል ጸሐፊ ቁጥሩ ከ፲፪ቱ ሐዋርያት ውስጥ የሆነ ስሙ ማቴዎስ የተባለ ሰው ነው። ይኸም ሰው ሌዊ እንደሚባል ሌላ ማስረጃ ይገኛል (ማርቆስ ፪·፲፬)

ይኸንም የተለያየ ስም ሊያገኝ የቻለው ለሐዋርያት ተግባር ከመጠራቱ በፊት ሌዊ ሲባል ቆይቶ ለሐዋርያነት ተግባር ከተጠራ በኋላ ማቴዎስ በመባሉ እንደሆነ ይነገራል ። ማቴዎስ ማለት ሀብተ እግዚአብሔር ወይም ጸጋ እግዚአብሔር ማለት ነው ። የዚህ ሐዋርያ አባት ስም እልፍዮስ ይባላል፡ የያዕቆብ ዘይንእስ አባት ስምም እልፍዮስ ይባላል ፤ እንዲሁም የጌታ ወንድም እየተባለ የሚጠራው የያዕቆብ አባትም እልፍዮስ ይባላል ስለዚህ የ፫ቱም ሐዋርያት አባት አንድ መሆኑ ይሆን የሚል ግምት አለ ። እልፍዮስ በሚለው አንፃር ደግሞ ቀለዮጳ የሚል ይገኛል ። እልፍዮስና ቀለዮጳ ከአረማይክ ወደ ግሪክ ሲተረጐም የፊደል መሳሳት እንጂ አንድ እንደሆነ ይገመታል ፤ እልፍዮስ የሚለው ስም ግን አወዛጋቢ ሁኖ ይገኛል ይሁን እንጂ እንደማጠቃለያ ሁኖ የሚነገረው የ፫ቱም ሐዋርያት አባቶች የተለያዩ እልፍዮሶች እንደሆኑ ነው ።

በኛ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት ደግሞ የማቴዎስን አባት ዲቁ ይለዋል ፤ እናቱን ደግሞ ካሪትያስ ይላታል (መቅድመ ወንጌል) ።

ይኸ ሐዋርያ ጥሪውን አክብሮ ጌታን ተከትሎ ከመሔዱ በፊት ሀብቱን አዘጋጅቶ ለደሀ የሚሰጠውን መጽውቶ ፤ ጌታን በክብር ግብር አግብቶ ወዳጆቹን ሁሉ ጠርቶ ሁሉንም ተሰናብቶ ወደኋላ እንዳይመለስ ሁኖ የሔደ ሐዋርያ ነው ። በዚህም መሠረት ፫ ዓመት ሙሉ ከጌታ ሳይለይ አብሮ ሲወጣና ሲወርድ ሲማር ቆይቷል ።

ከጌታ ትንሣኤም በኋላ ከ፲፪ቱ ቤተሰብ ጋር እስከ ዕርገቱ ድረስ እንደነበር ቅ·ሉቃስ ያስረዳናል (የሐ·ሥራ ፩·፲፫) ።

ሐዋርያት በየሀገረ ስብከታ





www.ethiopianorthodox.org

ቸው ሲበተኑ ማቴዎስም ለስብከተ ወንጌል እንደሔደ ይነገራል ፡ ይሁን እንጂ የማቴዎስ ሀገረ ስብከት የት እንደሆነ እስካሁን ግልጥ አይደለም ። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች በኢትዮጵያ እንደሰበከ ይጽፋሉ ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ የሚለውም ስም በዚያን ጊዜ ሰፊ ስለነበረ በየትኛው ክፍል ገብቶ እንደሰበከ ግልጥ የሆነ ነገር እስካሁን አልተገኘም ። አንዳንዱ ደግሞ በፍልስጥኤም በሶርያ ፥ በፋርስ ፥ እንደሰበከ ይናገራሉ ። ሌሎች ደግሞ ሕንድ ድረስ ሒዶ እንደሰበከ በዚያም እንደሞተ ይናገራሉ ሕንድ የሚለውን ስም ግን ለዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሰጥተው የሚናገሩ ሊቃውንት በብዛት ስላሉ ማቴዎስ የኢትዮጵያችን መምህርና ሰባኪ ወንጌል እንደሆነ አስፋፍተው ይናገራሉ ። አስረጅም ሲሰጡ የእርሷን ንግሥት ሕንደኬ እያሉ ይጠሯት ነበር ቅፍሬምና ጦስንም የሕንድ ኤጲስቆጶስ እያሉ ይጠሩታልና ። ይሁን እንጂ በኛ ትውፊት ውስጥ ማቴዎስም ሆነ ሌሎች ሐዋርያት በኢትዮጵያ እንደሰበኩ የሚናገር የለም እንዲያውም እንደ ክብር ሁኖ የሚነገረው ማንም ሐዋርያ ሳይሰብከልን ሳያስተምረን አምነን እንደተገኘን ነው ።

በሌላ ትውፊት ደግሞ ማቴዎስ ኢትዮጵያ ወደ ምትባል ሀገር ሒዶ የካህናት ከተማ በምትባል ሲሰብክ ብዙ ተአምራት ሲያደርግ ኑሮ በቤተ መንግሥቱም ታዋቂ ሁኖ ንጉሣዊ ቤተሰብን ሁሉ አሳምኖና አጥምቆ የጣዖት ካህን የነበረውን ኤርሚስ የተባለውን ጽጽስና ሰጥቶ እንደሔደ ገድለ ሐዋርያት የተባለው መጽሐፍ ይናገራል ።

ሌላው ትውፊታችን ደግሞ "ወኮነ ስምዐ በሀገረ ልብዕክራውትረ በዕብን አመ ፲ወ፪ ለጥቅምት ወተቀበረ በቅርጣግና ዘቲማርያ ሲል ይገኛል" (መቅድመ ወንጌል) ።

የሆነው ሁኖ ማቴዎስ በፍልስጥኤም ሳለ ወንጌሉን ከአይሁድ ውስጥ ለአመኑ አይሁድ መማሪያ፥ መመሪያም ይሆናቸው ዘንድ ጻፈላቸው ። ለዕብራውያን የጻፈ እንደመሆኑ የጻፈበት ቋንቋ አረማይክ እንደሆነ ይነገራል ምክንያቱም ዕብራውያን በዚያን ጊዜ ይናገሩበት የነበረው ቋንቋ የዕብራይስጥ ዲያሌክት የሆነ አረማይክ የተባለ ነበር ጌታም ሲናገር ሲማርም ያደገበት ቋንቋ ይኸው እንደ ነበር ይነገራል ።

ማቴዎስ ወንጌሉን በአራማይክ መጻፉን ለመጀመሪያ ጊዜ የጠቆመን ፓፒያስ የተባለ የቤተ ክርስቲያን አባት ነው ፡ እርሱም እንዲህ ሲል ይናገራል ማቴዎስ ወንጌሉን ሲጽፍ የጌታ ቃል የሆነውን የዕብራይስጥ ዲያሌክት በሆነው በአረማይክ ቋንቋ ጻፈ ይኸንም ይዘው ሊቃውንት "የጌታ ቃል" የሚለውን በተለያየ አስተያየት ይወስዱታል ፡ ማለት በሙላ ወንጌሉን ሳይሆን አልፎ አልፎ ብሎ የሚገኘውን የጌታ ቃል የሆነውን ብቻ በዕብራይስጥ እንደጻፈ ይናገራሉ። ሌሎች ደግሞ በሙላ ወንጌሉን የጌታ ቃል እንደሆነ አድርገው በሙላ ወንጌሉን በዕብራይስጥ እንደጻፈው ይነገራል ። ሌላው ትውፊት ደግሞ "ወወጠነ ጽሒፈ ዝንቱ መጽሐፍ በፍልስጥኤም ወፈጸማ በሕንድ "ዕብራይስጣዊ" ይላል (መቅድመ ወንጌል) ይሁን እንጂ ወዲያው ወንጌሉ ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክኛ ተተርጉሟል ፡ ይኸንም የተረጎመው እንደኛ ትውፊት የሆነ እንደሆነ ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው ፡ እርሱም እንዲህ ሲል ያመጣዋል "ወለዛቲ ብሥራት ተርጕማ ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ በሀገረ ኤላንስ ወሰበከ ባቲ በሕንድ ወበኢየሩሳሌም" ሲል ያስረዳል (ትርጓሜ ወንጌል) በሌላው ቤተ ክርስቲያን ትውፊት እንደምንረዳው ግን ራሱ ማቴዎስ ወደ ጽርእ ቋንቋ እንደተረጐመው ነው ። ማቴዎስ ከጌታ ሳይለይ የኖረ እንደመሆኑ የጻፈው ያየውንና የተማረውን ነው ፡ ስለዚህም የዐይን ምስክር ይባላል ።

የማቴዎስ ወንጌል ብዙውን ጊዜ ወደ ብሉይ ኪዳን ያዘነበለ ሁኖ ይገኛል ፡ ስለዚህም እስራኤላውያን አክብረው ተቀብለውት እንደነበር ያጠያይቃል ።

የማቴዎስ ወንጌል ዘግይቶ እንደተጻፈ ከውስጡ የሚጠቁሙ ምልክቶች በመገኘታቸው ብዙ ሊቃውንት ከሌሎቹ ወንጌላት ይልቅ ዘግይቶ እንደተጻፈ ይናገራሉ ፡ ይሁን እንጂ ከወንጌላት ቀዳሚ ሁኖ እንዲገኝ ከአስደረጉት ምክንያቶች አንደኛው ከብሉይ ኪዳን ውስጥ ብዙ ስለሚጠቅስ የተስፋውን ቃል በጣም አጉልቶ ስለሚናገር ፡ ትንቢቱን በሁኔታ በተፈጸመ ነገር ስለሚገልጠው ለብሉይና ለሐዲስ ኪዳን መገናኛ መያያዣ ይሆናል በማለት ከሌሎቹ ወንጌላት ቀድሞ በመጀመሪያ እንዲጠረዝ ሆነ ። እንዲሁም ከብሉይ ወደ ሐዲስ መሸጋገሪያ ይሆናል ፡ የብሉይ መጨረሻ የሐዲስ መጀመሪያ ይሆናል በማለት በቀዳሚነቱ እንዲጠረዝ ሆነ ።



የማቴዎስ ወንጌል ዋና ዓላማው ድኅነት ለእስራኤል ነው ፡ አዳኙም ኢየሱስ ነው ፡ ይኸውም ሊሆን የሚችለው ከእስራኤል ቤት በተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ለማለት ነው ። ስለዚህም ወንጌሉን ሲጀምር "መጽሐፈ ልደቱ ለኢየሱስ ይላል በአንድ በኩል የኢየሱስን ሰው መሆን ሰብአዊ ልደቱን ይናገራል ፡ በሌላ በኩል ግን የሐዲስ ኪዳን ልደትን እንደገለጠው ሁሉ ማቴዎስም እንዲሁ መጽሐፍ ልደቱ በማለት ጀመረ ።

ብሉይ ኪዳን የሰማይንና የምድርን የሌሎችንም በውስጣቸው የሚገኙትን ፍጥረታት ልደት ይናገራል ፡ ሐዲስ ኪዳን ግን ሰማያዊው ምድራዊ ሆነ ፡ ምድራዊውም ሰማያዊ ሆነ ሲል በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ለማጥፋት ተናገረ ።

ብሉይ ኪዳን የመጀመሪያውን የሞት ምክንያት የሆነውን የአዳምን ተፈጥሮ ይናገራል ፡ ሐዲስ ኪዳን ደግሞ ለሕይወት ምክንያት የሆነውን የ፪ኛውን አዳም ልደት ይናገራል ። ክርስቶስ ከሥጋችን ሥጋን ከደማችን ደምን ነፍስንም ነስቶ ፍጹም ሰው ስለሆነ ፪ኛው አዳም ይባላል በተለይም እስራኤላዊያን ይመጣል ብለው ተስፋም አድርገው ይጠብቁት የነበር መሢሕነቱን አምነው ከዳዊት ዘር ተወልዶ በዳዊት ዙፋን ተቀምጦ ለዘለዓለሙ ነግሦ እንደሚኖር ነበርና ። በዚህም ምክንያት ወንጌላዊው የክርስቶስን ወልደ ዳዊትነት በመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ላይ "ወልደ ዳዊት" በማለት አስተዋወቀ ።

እንዲሁም የብዙ ሕዝብ አባት እንደሚሆን ለመግለጥ ሲል የብዙ ሕዝብ አባት እየተባለ የሚጠራው የአብርሃም ልጅነቱን "ወልደ አብርሃም" በማለት በዚሁ መሥመር ላይ ገልጦት እናገኘዋለን ።

ማቴዎስ የክርስቶስን ሐረገ ልደት ሲቆጥር በ፫ ደረጃ መድቦ አቀረበው ፡ ይኸውም ፩ ከአብርሃም እስከ ዳዊት ፡ ፪ ከዳዊት እስከ ባቢሎን ምርኮ ፡ ፫ ከባቢሎን ምርኮ እስከ ክርስቶስ ያለውን ለይቶ አቀረበ ።

ማቴዎስ ወንጌልን ለመጻፍ የተነሣበት ዋናው ዓላማ ከዕብራውያን ወስጥ ክርስቲያን የሆኑትን ለማስተማርና የተማሩትም በዚያው ጸንተው እንዲኖሩ ለማድረግ ነው ፡ ስለዚህም ሲጀምር " መጽሐፈ ልደቱ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ ዳዊት ወልደ አብርሃም" ሲል ክርስቶስ ተስፋና ትንቢት ከተናገረላቸው ሱባዔ ከተቆጠረላቸው ከአብርሃምና ከዳዊት ዘር የተወለደ ነው ለማለት በእስራኤል ዘንድ የተወደዱትን አበው በመጥራት ጀመረው ። አስተጋብዕያነ መጻሕፍት ግን "ብሥራተ ማቴዎስ ሐዋርያ አሐዱ ከእም ፲ ወ ፪ ሐዋርያት" ብለው አርእስት እንደሰጡ ይነገራል ። ይኸን ርእስ አድርገው እንደሰጡ በኛ ትውፊት የሚገመተው ፫፻፲፰ ሊቃውንት ናቸው ። ይሁን እንጂ ይኸን የመሰለ ርእስ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት አይገኝም ቀጥሎም ለመጻሕፍት ሁሉ አርእስት የተሰጡ ከ፫፻፳፭ ዓ ም በፊት ፫፻፲፰ ሊቃውንት ከመነሣታቸው በፊት ነው ።

የሆነው ሁኖ ጌታ የተናገረው ያስተማረው ፡ ማቴዎስ የጻፈው

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ጥቅሶች

(ከገጽ ፳፱ የዞረ)

፫ኛ ይህም መዋሐድ ውሃ በእስፖንጅ (በሰፍነግ) እንደሚመጠጥ ትስበእት በመለኮት ወይም መለኮት በትስበእት በመካተት እንደ አውጣኪ አነጋገር መለኮት ከተዋሐደው በኋላ ረቀቀ ማለታችን አይደለም ።

፬ኛ ወይም ደግሞ በአምላክነትና በሰውነት መካከል ሁለትነት (ምንታዌ) አለ ማለት አይደለም መለኮት ከትሰበእት ጋር ከተዋሐደ በኋላ ሁለት ዓይነት ባሕርያት የሉትም ። አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው እንጂ ።

ስለዚህም መለኮት የሚሠራውን ሁሉ ሥጋም አብሮ ተዋሕዶ በመሥራት ላይ በመሆኑ አንዱ ከሌላው ተነጥሎ አይታይም ። ለምሳሌ መራብ መጠማት ተይዞ መታሠርና መስቀል መሸከም ተሰቅሎ መሞት መቸንከርና በጦር መወጋትን የመሳሰሉትን ጻዋትወ መከራ ሁሉ በመቀበል ረገድ መለኮትም አብሮ ተፈትኗል ። ይኸውም አንጥረኞች የጋለውን ብረት በመዶሻ በሚቀጠቅጡበት ጊዜ ከብረቱ ጋር የተዋሐደው እሳትም አብሮ እንደሚቀጠቀጥ ማለት ነው ወይም በጋለ ብረት ላይ የሚያርፍ የዐሐይ ብርሃን ከብረቱ ጋር አብሮ እንደሚመታ መለኮትም ከተዋሐደው ትስብእት (ሥጋ ሰብእ) ጋር አብሮ ተደብድቦ የሞትን ጽዋ ተቀብሏል ወደ ከርሠ መቃብር አብሮ ወርዶአል ፡ እንደ

(ከገጽ ፳፪ የዞረ)

ወንጌል መሆኑን አምነን ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ ትርጉሙን ለመተርጐም እንጀምራለን ።

ይቀጥላል



www.ethiopianorthodox.org

# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ
# አምስቱ የምሥራቅ (የኦርየንታል) ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ

ከመ/ሉሌ መልአኩ

ክርስትና ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ በመላው ዓለም የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት በ፬፻፶፩ ዓ/ም እስከተደረገችው የኬልቄዶን ጉባኤ ድረስ በእምነት አንድ ነበሩ ። ሆኖም እንደነአርዮስ ፣ መቅዶንዮስ ፣ አቡሊናርዮስ ፣ ንስጥሮስና አውጣኪስ የመሳሰሉ ከሐዲዎች ከቀጥተኛው የክርስትና እምነት ባፈነገጡ ቁጥር በየጊዜው በተደረጉት ጉባኤዎች በተቀመጡት አባቶች ከነተከታዮቻቸው ተወግዘው ተለይተዋል ።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደ ምንመለከተው የዓለም ቤተ ክርስቲያን ለመጀመሪያ ጊዜ በእምነት ለሁለት የተከፈለችው በ፬፻፶፩ ዓ/ም በተደረገችው በኬልቄዶን ጉባኤ ነው ። ይኸውም የካቶሊክና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት ሲሉ ፣ የተዋሕዶ እምነትን የሚከተሉት የአምስቱ አብያተ ክርስቲያናት አባት የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ መሆኑን ፣ መለኮትና ትስብእትም ያለመለያየት ፣ ያለመቀላቀል ፣ ያለመለወጥ ስለተዋሐዱ አንድ አካል ፣ አንድ ባሕርይ ፣ አንድ ፈቃድ አንድ ግብር ነው በማለት ቀጥተኛውን የተዋሕዶ እምነት ካስረዳ በኋላ በዚሁ እምነት ላይ ሁለቱም ወገኖች ለመስማማት ባለመቻላቸውና ተወጋግዘው በመለያየታቸው ፣ እስከዚያ ጊዜ ድረስ አንድ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ከሁለት ላይ ተከፈለች ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከአምስቱ የተዋሕዶ እምነት ተከታዮች አብያተ ክርስቲያናት አንዷ ስለሆነች ምእመናን ምንም እንኳ በአጠቃላይ የመላ አብያተ ክርስቲያናትን ታሪክ በመጠኑም ቢሆን ማወቅ ቢያስፈልጋቸውም ቅሉ ፣ በቅድሚያ በእምነት መሰሎቻችን የሆኑትን የእስክንድርያን (የግብጽን) ፣ የኢትዮጵያን ፣ የሶርያን (የያዕቆባዊትን) ፣ በደቡብ ህንድ የማላባርንና (የቶማስንና) የአርመንን አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ጠንቅቀው ማወቅ ተገቢ ነው ። የእነዚህም አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ከጥር ፯ እስከ ፲፫ ቀን ፲፱፶፯ ዓ/ም (እንደ ኢ.ት.አቆጣጠር) አዲስ አበባ ውስጥ ታሪካዊ ጉባኤ አድርገው በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይተዋል ።

በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን እየተዘጋጀ በሚወጣው በዚህ መጽሔት ቀለልና አጠር ባለ አኳኋን በተከታታይ የአምስቱን እኅትማማች አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ እያዘጋጀሁ ለመጻፍ እሞክራለሁ ። ይህ ታሪክ በትክክል ተቀነባብሮ ለምእመናን እንዲቀርብ የማድረጉ ኃላፊነት የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ምሁራን ሁሉ ስለሚመለከት በጽሑፉ ውስጥ ከበድ ያለ ስሕተት ቢገኝና በቀላሉ ሊታለፍ የማይገባው ክፍል ቢኖር አንባቢያን በመጽሔቱ አዘጋጅ በኩል ገምቢ የሆነ ምክራቸውንና አስተያየታቸውን ቢለግሡኝ እርማቱ በሚከተለው እትም ተስተካክሎ ሊወጣ ይችላል ።

ይህንን ጽሑፍ ሳዘጋጅ የተጠቀምሁባቸው አብዛኞቹ መጻሕፍት በውጭ ሀገር ቋንቋ የተጻፉ ስለሆኑ ፣ በጽሑፉ ውስጥ የሰፈሩ ዓመተ ምሕረቶች እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ናቸው ። ወደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ለመለወጥ ሲያስፈልግ ከመስከረም እስከ ታኅሣሥ ፰ ዓመት ከጥር እስከ ጳጉሜ ፯ መቀነስ ነው ።

ከዚህ ቀጥለን የአምስቱን አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ባጭሩ እንመለከታለን ።

## ፩ኛ/ የእስክንድርያ (የግብጽ ፣ የኮፕት) ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደ ምንመለከተው የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ በሆኑ በቢዛንታይን ነገሥታትና የእስልምና እምነት ተከታይ በሆኑ ቅኝ ገዥዎች ቀንበር ሥር ለብዙ ዘመናት በመማቀቋ ምክንያት የምእመናኖቿ ቁጥር አንሶ ፣ ተዳክማና ኮስሳ የምትታየው የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በ፬፻፶፩ ዓ/ም እስከተደረገችው እስከ ኬልቄዶን ጉባኤ ድረስ ከሌሎች የዓለም አብያተ ክርስቲያናት በይበልጥ ለክርስትና መጠናከርና መስፋፋት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርጋለች ። ይኸውም በቅዱስ ማርቆስ ተመሥርታ በክርስቲያኑ ዓለም መጀመሪያ የነበረችውን ዝነኛዋን የእስክንድርያን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ከፍታ በማስተማር ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶችን አፍርታለች ። ግብጽ ውስጥ ኒትሪያንና አስቄጥስ በተባሉት በአባይ ወንዝ ዳር በሚገኙት በረሃማ ቦታዎች በእነአባ እንጦንስ መቃርስና አሞንዮስ አማካይነት የብሕትውናን ኑሮ በመመሥረት በዓለም ለሚገኙት ገዳማት መመሪያ የሆነ መሠረት ጥላለች ። እንደነ ቅዱስ አትናቴዎስና ቄርሎስ የመሳሰሉት ዝነኞችና ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶችና ሊቃውንትን አፍርታለች ። የወንጌል መልእክተኞቿንም ወደ ኑብያ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ፔንዳፖሊስ (ሊቢያ) ፣ ዐረብያ ፣ ህንድ ወዘተ ልካ በትጋት በመስበክና በማስተማር ለክርስትና መስፋፋት ጥራለች ። መናፍቃንም በተነሡ ቁጥር በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት መሠረት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ቀጥተኛ እምነታችንን የወሰኑትን የኒቅያን ፣ የቁስጥንያንና የኤፌሶን ጉባኤዎች በሊቀ መንበርነት የመሩ የእስክንድርያ ፓትርያርኮች ነበሩ ።

ከላይ የተጠቀሰችው መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ፣ ስላፈራቻቸው የቤተ ክርስቲያን አባቶችና ሊቃውንት ለወደፊት ሰፋ አድርገን እንመለከታለን ።

የግብጽ ክርስቲያኖች በቢዛንታይን ነገሥታት ፣ እስልምናን በሚከተሉ ዐረቦች ፣ ቱርኮች ወዘተ የቅኝ አገዛዝ ቀንበር ሥር በመውደቅ ለዘመናት ከፍ ያለ መከራና ሥቃይ ቢቀበሉም ፣ የካህናቶቻቸውና የምእመናኖቻቸው ቁጥር እየቀነሰ (እየመነመነ) ቢሄድም ቅሉ ፣ ካህናቱ ለዘመናት ቀጥተኛ እምነታቸውን በመጠበቅ ምእመናንን በትጋት ሲያስተምሩ ፣ ሲንከባከቡና ሲያጽናኑ ኖረዋል ። አሁንም በተጠናከረ ሁኔታ ምእመናንን በመንከባከብ ላይ ናቸው ።

በሃያኛው ክፍለ ዘመን የተነሡ የግብጽ ገዥዎች በሀገሪቱ ለሚገኙ (ለሚኖሩ) የተለያየ ሃይማኖት ተከታዮች መጠነኛ የአምልኮ ነፃነት ስለሰጡ ዛሬ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ኮሌጅና ማሠልጠኛዎችን ከፍታ ካህናትን በብዛትና በጥራት ታሠለጥናለች ። ሠልጥነው በሚወጡትም ምሁራን አማካይነት ምእመናንን በትጋት ስለምታስተምርና ስለምትንከባከብ የምእመናኖቿ ቁጥር እየጨመረ መጥቷል ። ከሀገሯ ውጭም በሱዳን ፣ በኩዌት ፣ በደቡብ አፍሪካ ወዘተ አብያተ ክርስቲያናት መሥርታ ወንጌልን ታስተምራለች ።

ከኬልቄዶን ጉባኤ ጀምሮ ክርስቲያኖች በእምነትና እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ በሚሉ ምክንያቶች በየጊዜው እርስ በእርሳቸው እየተወጋገዙ ስለተለያዩ ፣ ይህንኑ በማጥበብ የተለያየ እምነት በሚከተሉ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ኅብረት ተመሥርቶ ወንጌልን በአንድነት ለማስፋፋት በማሰብ በሃያኛው ክፍለ ዘመን ለተቋቋመው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን መሥራች አባል ናት ።

ከዚህ በታች ስለ ግብጽ (እስክንድርያ) ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት ከቤተ ክርስቲያኒቱ ጋር የተቆራኙትንና ሊወሱ የሚገባቸውን ዋና ዋና ነጥቦች (ርእሶች) እንመለከታለን ።

### ሀ/ ቅዱስ ዮሴፍ ከሄሮድስ በመሸሽ እመቤታችንንና ጌታን ይዞ ወደ ግብጽ ያደረገው ስደት ።

ግብጽ ውስጥ ክርስትና በወንጌላዊው ማርቆስ ከመሰበኳ ብዙ ዓመታት ቀደም ብሎ በማቴዎስ ወንጌል ፪፡፲፫—፲፰ በተጻፈው መሠረት ቅዱስ ዮሴፍ ጌታንና እመቤታችንን ይዞ ከሄሮድስ ግዛት ውጭ ወደ ነበረችው ወደ ግብጽ በተሰደዱበት ወቅት የግብጽ ክርስቲያኖች ጥንታውያን አባቶቻቸው ጌታንና እመቤታችንን ተቀብለው የማስተናገድ ዕድል ማግኘታቸውን እንደ ታላቅ በረከት ይቆጥሩታል ። እንዲሁም ቅዱስ ዮሴፍ ፣ እመቤታችንና ጌታ በጉዞ ላይ ሳሉ ባረፉባቸውና ግብጽ ውስጥ በኖሩባቸው ቦታዎች ላይ የቅዱስ ሰርግዮስን ፣ የእመቤታችንን ወዘተ አብያተ ክርስቲያናት በመሥራትና ገዳማት በመመሥረት ለነሱ ያላቸውን የአክብሮት ስሜት ገልጸዋል።

ቅዱስ ዮሴፍ ጌታና እመቤታችን ወደ ግብጽ ሲጓዙ በነበረበት ወቅት በመንገዳቸው ከአጋጠሙአቸው ሁለት አደጋዎች እንዴት እንደዳኑ የሚነገሩ አፈ ታሪኮች አሉ ። የመጀመሪያው አፈ ታሪክ ዮሴፍና እመቤታችን ሕፃኑን ጌታን ይዘው ሲጓዙ በመንገድ ቀማኞች ደርሰው ለመቀማት አቆሙአቸው ። ከቀማኞቹ አንዱ መንገደኞቹን ገድሎ የያዙትን ጥሪት ለመውሰድ ሲከጅል ዲስማስ የተባለው ቀማኛ ለሕፃኑ ለጌታ ሕይወት በመራራት ፣ በጌታም ሆነ በዮሴፍና በማርያም ላይ





www.ethiopianorthodox.org

ከልክሎ የሚበሉት ከሰጣቸው በኋላ መንገዳቸውን በሰላም እንዲቀጥሉ አደረጋቸው ። ይህም ዲስማስ የተባለው ቀማኛ ከጊዜ በኋላ በጌታ ቀኝ በኩል ተሰቅሎ ሳለ "ጌታ ሆይ ፤ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ" ሉቃ ፳፫፥፵፪ ብሎ በመለመን ከአዳም ቀድሞ መንግሥተ ሰማያት የገባው ነው ይባላል ። ሁለተኛው አፈታሪክ ደግሞ ዮሴፍ ፤ ጌታና እመቤታችን ሲጓዙ ውለው ስለደከሙና ስለመሸባቸው ሌሊቱን ለማሳለፍ ከአንድ ዋሻ ውስጥ ገብተው ዐረፉ ። ጊዜው ብርድ ስለነበር ቅዝቃዜው ሲያንቀጠቅጣቸው ነበር ። በተለይ የሕፃኑን በብርድ መኮራመት የተመለከተች ሽረሪት ትንሽ ሙቀት ይሰጠዋል ብላ የዋሻውን መግቢያ በር በድሯ ዘጋችው ። ጌታን ይዘው ለመግደል በሄሮድስ ከታዘዙት ወታደሮች ጥቂቶቹ ይከታተሉአቸው ስለነበር እነ ዮሴፍ ሲመሽባቸው ሌሊቱን ለማሳለፍ ከአንድ ዋሻ ደርሰው አንዱ ወታደር ለመፈተሽ ዘው ሲል ፤ ጓደኛው ሞኝ ነህ እንዴ ? የዋሻው በር በሸረሪት ድር ተተብትቦ እያየኸው ለምን ትደክማለህ? በቅርብ ጊዜ ሰው ቢገባበት ኖሮ ድሩ ይበጣጠስ ነበር ስላለው ፤ እውነቱ እኮ ነው ብሎ ተመለሰ ። በዚህ በሸረሪቷ ድር ምክንያት የጌታ ሕይወት ከሞት ተረፈ ይባላል ።

ጌታ የግብጽን ምድር ከረገጠበት ጊዜ ጀምሮ በየመቅደሶቹ የነበሩ ጣዖታት ሊያመልካቸው በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት እየወደቁ ተሰባብረዋል ። በተለይም ሕፃኑ ኢየሱስ ሔሊዮፖሊስ ከምትባለው የአሕዛብ መቅደስ ሲገባ ከመቅደሱ ውስጥ የነበሩት ፫፻፷፭

ጥናትና ጥቅሶች

(ከገጽ ፲፱ የዞረ)

ተጻፈነም እሳት ሶስት መዓልትና ሶስት ሌሊት ቆይቶ በመነሣቱ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ ተብሎ ተጻፈ (፩ ጴጥ ፫፡፲፱) ።

የነገረ ሞቱ ትርጉም

ኢሳ ፶፫፡፭፡፮ እርሱ ስለመተላለፋችን ቆሰለ ስለበደላችንም ደቀቀ ፤ የደህንነታችንም ተግሣጽ በርሱ ላይ ወደቀ ፤ በርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን ፤

— ፪ ቆሮ ፭፡፳፩ — እኛ የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ወይ በባሕርዩ በደል (ኃጢአት) የማይስማማውን ክርስቶስን እንደ በደለኛ ሆኖ እንዲቆጠር አደረገው ። ጴጥ ፫፡፲፰ ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር ያቀርበን ዘንድ ፈቅዶ እርሱ ጻድቅ ሆኖ

ጣዖታት ሊያመልካቸው በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት በተአምር ተንኮታኩተው ሲሰባበሩ የተመለከተው ሕዝብ በክርስቶስ አምኖ ክርስትናን እንደተቀበለ ይተረካል ።

ሦስቱ እንግዶች ግብጽ ውስጥ እስከሄሮድስ ሞት ድረስ መሰንበታቸው እንጂ የቆዩበት ጊዜ ልክ አልተገለጸም ። ሆኖም አንዳንድ ሊቃውንት ስድስት ወራት ቆዩ ሲሉ ፤ ሌሎች ደግሞ ከሁለት እስከ አራት ወይም ስድስት ዓመት ያህል ቆይተዋል ይላሉ ። የኢትዮጵያ ሊቃውንት ግን ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ቆዩ ይላሉ (ወንጌል ቅዱስ ። ከቀድሞ አባቶች ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ንባቡና ትንጓሜው ። ፲፱፻፷፪ ዓ ም ገጽ ፲፩)

ይቀጥላል

ምክንያት አንድ ጊዜ ሞቶአል ።

ዮሐ ፪፡፪ ክርስቶስ የኃጢአታችን ሁሉ ይቅርታ ነው ።

ራእ ፭፡፱ አንተ የመጽሐፉን ጥቅል ልትወስድ ይገባሃል ። ምክንያቱም አንተ ተገድለህ ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ከወገንና ከሕዝብም ሁሉ በደምህ የእግዚአብሔር ሰዎችንዋጅተሃል ፤ ለአምላካችንም መንግሥትና ካህናት የሆኑ ዘንድ ለዚህ አብቅተሃቸዋል

ክርስቶስ ሁሉን አዋቂና በሁሉም ስፍራ ምሉእ ስለመሆኑ ፤

ዮሐ ፪ ፳ ፳፭ ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ስለነበር ስለሰው ሁኔታ ማንም እንዲመስክርለት አያፈልግም ነበር ።

ዮሐ ፩ ፵፰ ኢየሱስም መልሶ "ፊልጶስ ሳይጠራህ" በፊት በበለስ ዛፍ (ተክል) ሥር አየሁህ" ኤር ፳፱ ፳፬)

ክርስቶስ ጸሎትንና ስግደትን የሚቀበል የባሕርይ አምላክ ስለመሆኑ

ዮሐዋ ፩ ፬ የሁሉን ልብ የምታውቅ አንተ ጌታ (ክርስቶስ) ሆይ ከሁለቱ አንዱን ሹም የሐዋርያት አገልግሎት ስፍራ እንዲቀበል የመረጥኸውን ከሁለቱ አንዱን ሹም የሐዋ ፯ ፶፱ እስጢፋኖስ ኢየሱስ ሆይ ፤ ነፍሴን ተቀበል" ብሎ ሲጮህ በድንጋይ ይደበድቡት ነበር ፤ ተንበርክኮም "ጌታ ሆይ ይህን ሁሉ ኃጢአት ዕዳ በደል አድርገህ አትቁጠርባቸው ብሎ በታላቅ ድምጽ ጮኸ ።

ማቴ ፲፬ ፴፪ በታንኳይቱም የነበሩት በዕውነት የእግዚአብሔር ነው ብለው ሰገዱለት ።

(ወደ ገጽ ፫ የዞረ)



# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ጥቅሶች

ራስን መሥዋዕት በማድረግ ሌሎችን ማገልገል

ማር ፰፡፴፬ ፴፭ ሕዝቡንም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ጠርቶ እንዲህ አላቸው እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ ፤ ሕይወቱን ሊያድን (ሊያተርፍ) የሚወድ ቢኖር የሚያጠፋ ግን ያገኛል። ሰው ዓለምን ቢገዛ ቢነዳ ነፍሱን ግን ቢያጠፋ ምን ይረባዋል? ምንስ ይጠቅመዋል ፤

፪ ቆሮ ፭ ፲፭ እርሱ ስለሁሉ ሞተ በሕይወትም ያሉት ስለነርሱ ለሞተውና ለተነሣው ክርስቶስ እንጂ ፤ ወደፊት ለራሳቸው የሚኖሩ አይሆኑም ። ሮሜ ፲፬ ፯

ዕውነተኞች አማኞች የሚያገኙት ሰማያዊ ዋጋ (ክብር)

፩ጴጥ ፪ ፯ ፰ ወርቅ በእሳት እንደሚፈተን ከሚጠፋ ወርቅ ይልቅ አብልጦ የከበረ እምነታችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ለምስጋና ለክብር ለውዳሴም ይሆንላችሁ ዘንድ አሁን ለጥቂት ጊዜ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል ፤ እርሱንም ሳታዩት እንኳ ትወዱታላችሁ ፤ አሁንም ምንም ባታዩት በርሱ አምናችሁ የነፍሳችሁን መዳን ተስፋ ስለአገኛችሁ (በሰብአዊ ቋንቋ) ሊናገሩት በማይቻል ክብር በሞላበት ሐሴት ደስ ይበላችሁ ።

ራእ ፯ ፲፯ ፲፯ ከዚያም በኋላ

ከመ አእ መክብብ አጥናው

መራብና መጠማት አይደርስባቸውም ፤ የፀሐይም ትኩሳት ሁሉ አይወርድባቸውም በዙፋኑ ላይ ያለው በጉ ዕረኛቸው ይሆናል ፤ ወደ ሕይወትም ውሃ ምንጭ ይመራቸዋልና እግዚአብሔርም ዕንባቸውን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል

ቅዱስ መጽሐፍ

፩ ጴጥ ፩ ፳፭ የእግዚአብሔር ቃል ለዘለዓለም ይኖራል ፤ ይም ቃል አስቀድሞ የተሰበከላችሁ ወንጌል ነው ።

፪ ጴጥ ፩ ፳ ፳፩ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኘውን ማንኛውንም ትንቢት ማንም ሰው በራሱ ግላዊ ፈቃድ እንዲያስፈልገው መተርጐም አይችልም ምክንያቱም ፤ ትንቢት ከቶ ከሰው ፈቃድ የመነጨ አይደለም ፤ ነገር ግን ቅዱሳን ሰዎች ከእግዚአብሔር ተቀብለው ተናገሩት እንጂ ።

የሚያስገኘው ጥቅም

መዝ ፩፻፲፰ ፻፴ የቃልህ ትርጉም ብርሃንን ይሰጣል ፤ ሕጻናትንም አስተዋዮች ያደርጋል ፤ ነገረ ቃልክ ያበርህ ወይ ጠብብ ሕፃናቱ ፤

ማቴ ፬ ፬ ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም ፤ እግዚአብሔር በሚናገረው ቃል ሁሉ እንጂ ።

ሮሜ ፲፭ ፬ ሰው በቀድሞ ዘመናት የተጻፈው ቃል ሁሉ እኛ ልንመከርበትና ልንገሠጽበት የተጻፈ ነው ። ይኸውም ከቅዱሳት መጻሕፍት በሚገኘው የመጽናናት ተስፋ ጸንተን እንድንኖር ነው ።

ኢፌ ፮ ፲፯ የእግዚአብሔርን መር ዕቃ የደኅንነትን ራስ ቁር ደፍታችሁ የመንፈስን ሰይፍ ያዙ ዘውእቱ ቃለ እግዚአብሔር እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው ።

ጢሞ ፫ ፲፭ ከልጅነትህ ጀምሮ ቅዱሳት መጻሕፍትን አውቀሃል ። እነዚህም ቅዱሳት መጻሕፍት በኢየሱስ ክርስቶስ ወደሚገኘው ጸጋ የሚያደርስ ጥበብ መገኛዎች ናቸው ።

ዕብ ፬፡፲፪ የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና የሚሠራ ነው ፤ ሁለት አፍ ካለውም ሰይፍ ይልቅ የተሳለ ነው ነፍስንና መንፈስን ጅማትና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ የሚቆራርጥ ነው ። በልብ ውስጥ የተሠወረውንም አሳብና ምኞት ሁሉ መርምሮ የሚፈርድ ነው ።

የእውነተኛ እምነት ማረጋገጫ ምልክቶች ፤

ማቴ ፯ ፳ ፳፩ ከፍሬያቸው ታውቃችዋላችሁ ጌታ ሆይ ፤ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም ፤ ነገር ግን በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚፈጽም እንጂ ።

ዮሐ ፪፡፫ ትእዛዛቱን ጠብቀን ብንገኝ እርሱን እንደምናውቀው እርግጠኞች ነን ። ምዕ ፪ ፲፭

ይህን ዓለምና በዓለም ያለውን ነገር ሁሉ አትውደድ ዓለምን የሚወድ ፍቅረ እግዚአብሔር ሊኖረው አይችልምና ።

— ምዕ ፫ ፲፬ — ወንድሞቻችን ስለምንወድ ከሞት ወደ ሕይ



www.ethiopianorthodox.org

ወት እንደተሻገርን እናውቃለን ፡ ነገር ግን ፍቅር የሌለው ሰው በጨለማ ውስጥ ይኖራል ።

ምዕ ፬–፲፫ የርሱን መንፈስ ስለሰጠን እኛ በርሱ ጸን ተን እርሱም በእኛ አድሮ እንደሚ ኖር እናውቃለን ።

## ሕይወት ያለው ምግባር (በጎ ሥራ)

ማቴ ፭.፲፮ መልካም ሥራችሁን አይተው ሰማያዊ አባ ታችሁን ያመስግኑት ዘንድ ብርሃ ናችሁ በሰው ፊት ይብራ ።

ሮሜ ፲፪ ፲፫ ቅዱሳን የሆኑ አማኞች ወንድሞችን በችግራ ቸው እርዱ ፡ በእንግድነት የሚመ ጡትንም ተቀበሉ ።

ቆሮ.፲ ፴፩ ስትበሉም ሆነ ስትጠጡ የምትሠሩትን ሁሉ ለእ ግዚአብሔር ክብር አድርጉት ፡

ኤፌ.፪.፲ እግዚአብሔር አስ ቀድሞ ያዘጋጀውን መልካም ሥራ ሁሉ እንድንሠራ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት እንደገና የተ ፈጠረን የእግዚአብሔር ፍጥረ ቶች ነን ።

ቲቶ.፪.፲፬ ክርስቶስ ከዓ መፃ ሁሉ ሊያድነንና መልካም ሥራ በመሥራት ረገድ ትጉሆች ሆነን እንድንገኝ የርሱ ንጹሕ ሕዝብ ሊያደርገን ፈቅዶ ስለእኛ ራሱን ለሕመም ለሞት አሳልፎ ሰጠ ።

ያዕ ፪ ፳ አንተ ከንቱ ሰው በጎ ሥራ (ምግባር) የተለየው እም ነት ፍሬቢስ መሆኑን ታያለህን?

ቁጥር ፳፮ ነፍስ የተለየው ሥጋ ምውት እንደሆነ ከበጎ ሥራ የተለ የች እምነትም ራስዋ የሞተች ናት

## ትምህርተ ክርስቶስ (ክርስቶሎጂ)

(ክርስቶስን የማወቅ ትምህርት)

ቅድመ ዓለም የነበረ ስለመ ሆኑ፡

ሚክ· ፭·፪ አወጣጡ ከጥ ንት የሆነ እስራኤልን የሚጠብቅ መሥፍን ከእንቺ ይወጣል ።

ዮሐ.፩.፩.፲፰ በመጀመ ሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብ ሔር ዘንድ ነበር ቃልም እግዚአብ ሔር ነበር ። እግዚአብሔርን ከቶ ያየው የለም ፡ ከአባቱ ጋር የነበረና ያለ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አንድ ልጁ ብቻ ገለጠው እንጂ ።

ዮሐ.፰ ፶፰ ዕውነት ዕውነት እላችኋለሁ እኔ ከአብር ሃም በፊት ነበርሁ ።

## መለኮታዊ ስለመሆኑ (የባሕርይ አምላክነቱ)

ማቴ.፲፮ ፲፮ አንተ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ የሆ ንህ ክርስቶስ ነህ ።

ዮሐ.፭ ፳፩ ፳፫ አብ የሞቱትን እንደሚያስነሣና ሕይ ወትን እንደሚሰጣቸው ወልድም እንዲሁ ለፈለገው ሰው ሕይወትን ይሰጠዋል ፡ አብ በማንም ላይ አይፈርድም የፍርድን ሥልጣን ሁሉ ለወልድ ሰጥቶታል ። ይህ ንም ማድረጉ ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩ ወልድንም ያከ ብሩ ዘንድ ነው ።

ዮሐ.፲ ፴ እኔና አብ አንድ ነን ።

ምዕ.፲፬ ፯.፱ ኢየሱስም እንዲህ አለው ፊልጶስ ሆይ ይህን ያህል ጊዜ ከናንተ ጋር ስኖር አላወቅኸኝምን? እኔን ያየ አብን አየ ፡ ታዲያ አንተ እንዴት አብን አሳየን ብለህ ትጠይቃለህ?

## ወደ ዓለም የመጣበት ዓላማ

ማቴ.፩.፳፩ ስሙንም ኢየሱስ ትለዋለህ ፡ ምክንያቱም እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታችን ያድናል ።

ማቴ.፳፮ ፳፰ ይህ ስለ ብዙዎች የኃጢአት ሥርየት የሚ ፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ነው ።

ማር.፪.፲፯ እኔ ኃጥአንን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣ ሁም ።

ማር. ፲.፵፭ የሰው ልጅ (ክርስቶስ) ሊያገለግልና ሕይወቱ ንም ለብዙዎች ቤዛ አሳልፎ ሊሰጥ እንጂ ሊገለገል አልመ ጣም።

ሉቃ.፲፱.፲ የሰው ልጅ የጠፋውን ፈልጎ ለማግኘትና ለማ ዳን መጥቶአል ።

## የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ ዓለምን ለማዳን ስለመምጣቱ (የሥጋዌው ምሥጢር)

ዮሐ.፩.፲፬ ቃልም ሥጋ ሆነ ፡ በእኛም አደረ ። ማቴ· ፩· ፳፫ ስሙንም አማኑኤል ይሉ ታል ፡ አማኑኤል ማለትም እግዚ አብሔር ከእኛ ጋር ሆነ ማለት ነው ። (ታዲያ አምላክ ሰው ሆነ ወይም ሥጋን ለበሰ ስንል ፡

፩ኛ በመለወጥ አይደለም ፡ ይኸውም የሙሴ በትር ተለውጣ እባብ እንደመሆኑዋ አይደለም ። መለኮትና ትስብእት (ሰውነት) በፍጹም አንድነት ተዋሕዶው አምላክ ሰው ሰውም አምላክ ሆነ ማለት ነው እንጂ ።

፪ኛ መዋሐድ ሲባልም እንደ ውሃና ወተት ወይም እንደ ዘይትና ውሃ የመቀላቀልን ነገር የሚያሳይ ሳይሆን የሁለቱን (የመለኮትና ትስበእትን) ፍጹም አንድነት የሚገልጥ ነው ። (ወደ ገጽ ፲፱ ይዞራል)



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የሰብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ጸዋትወ ዜማዎችንና ትዳ ምችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ ቡ ን እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስተምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች ጋብ ት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ስምንት ብር በማስከፈል ይሰጣል ። ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፡

የስልክ ቍ.
የመልእክት ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org